የሰኞ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ

ገ/እግዚአብሔር ኪደ

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ ነሐሴ ፭ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.)፡- ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችን ከባረከችው በኋላ ምስጋናውን የጀመረው “ፈቀደ እግዚእ...” ብሎ ነው።

፭. በመቅድመ ወንጌል “ወአልቦቱ ካልእ ሕሊና ዘንበለ ብካይ ላዕለ ኃጢያቱ - በኃጢአቱ ከማዘን፣ ከማልቀስ በቀር ሌላ ግዳጅ አልነበረውም” እንዲል ጌታ ፭ ሺህ ከ፭፻ ዘመን በግብርናተ ዲያብሎስ ያዘን ይተክዝ የነበረ አዳምን ነጻ ያደርገው (ያድነው) ዘንድ ወደደ። ምድራዊ ንጉሥ የተጣላውን አሽከር “ሰናፊልህን (ልብስህን) አትታጠቅ፤ እንዲህ ካለ ቦታም አትውጣ” ብሎ ወስኖ ያግዘዋል። በታረቀው ጊዜ ግን ርስቱን፣ ጉልበቱን፣ ቤቱን፣ ንብረቱን እንደሚመልስለት ኹሉ ንጉሠ ሰማይ ወምድር እግዚአብሔርም “ጥንቱንም መሬት ነህና ወደ መሬት ተመለስ” /ዘፍ.፫፡፲፱/ ብሎ ፈርዶበት የነበረ አዳምን ይቅር ብሎ ወደ ቀደመ ቦታው ወደ ገነት፣ ወደ ቀደመ ክብሩ ወደ ልጅነት ይመልሰው ዘንድ ወደደ /ሉቃ.፳፫፡፵፫/።

ሊቁ (ቅዱስ ኤፍሬም) በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፱ ያለውን ኃይለ ቃል ሲተረጕምም እንዲህ ይላል፡- “ቸር ወዳጅ የኾነው እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ወዲያው እንደተሳሳቱ ፍርዱን አላስተላለፈባቸውም፤ ታገሣቸው እንጂ። ይኸውም ምሳረት ቸርነቱን ይለምኑት ዘንድ ነው። እነርሱ ግን አልለመኑትም። እግዚአብሔርም ምንም ሳይናገራቸው በገነት ውስጥ በእግር እንደሚመላለስ ሰው ኾኖ በድምፅ ብቻ መጥራቱን ቀጠለ። አዳምና ሔዋን ግን አሁንም አልመለስ አሉ። በመጨረሻም አምላክ ድምፁን ማሰማት ጀመር። ‘አዳምን ወዴት ነህ?’ ይላቸው ጀመር። አስቀድሞ በእግር እንደሚመላለስ ሰው ኾኖ በድምፅ ብቻ መጥራቱ መንገድ ጠራጊው ዮሐንስን እንደሚልክላቸው፣ ቀጥሎ ድምፅ አሰምቶ ወዴት ነህ ብሎ መፈለጉም ወልደ እግዚአብሔር ራሱ በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ኾኖ ሊያድናቸው እንደ ፈቀደ ያጠይቃል” ይላል /St. Ephrem the Syrian, Commentary on Genesis/።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ኦሪት ዘልደትን በተረጐመበት በ፶፯ኛው ድርሳኑ ላይ፡- “በዚህ ንግግሩ የእግዚአብሔር ከአእምሮ የሚያልፈውን ፍቅሩን እንመለከታለን። አንድ አባት ልጁ የማይረባውን ነገር በማድረግ ከክብሩ ቢዋረድም አባቱ እጅግ እንዲወደውና ወደ ቀደመ ክብሩ ይመልሰው ዘንድ እንዲደክም፤ እግዚአብሔርም ከሰው ልጆች ጋር ይህን የመሰለ ፍቅር ሲያሳይ እናስተውላለን። አንድ ሐኪም ወደ ታማሚው አልጋ ጠጋ ብሎ በሽተኛውን እንዲጠይቀውና አስፈላጊውን ኹሉ እንደሚያደርግለት፣ ሰው ወዳጁ እግዚአብሔርም ወደ አዳም ጠጋ ብሎ ሲያነጋግረው እንመለከታለን” ይላል።

ዳግመኛም በሌላ አንቀጽ “አዳም ሆይ ወዴት ነህ” ማለቱ፣ ለአቅርቦት መኾኑን ሲገልጥ፥- “አዳም ሆይ! ምን ኾንክብኝ? በመልካም ቦታ አስቀምጬህ ነበር፤ አሁን ግን ቦታህ ተለወጠብኝ። ብርሃን ተጐናጽፈህ ነበር፤ አሁን ግን ጨለማ ውስጥ አይሃለሁ። ልጄ! ወዴት ነህ? ይህ ኹሉ እንደምን ደረሰብህ? በአንተ ውስጥ ያኖርኩት መልኬ ማን አበላሽብኝ? በዚህ ያህል ፍጥነት የጸጋ ልብስህን ገፎ የጽልመት ልብስ ያከናነበህ ማን ነው? ውዴ! ባለጸጋ አድርጌ ፈጥሬህ አልነበረምን? ታድያ አሁን ድኽነት ውስጥ የከተተህ ማን ነው? ያን የግርማ ልብስህን ሰርቆ ዕራቁትህ ትኾን ዘንድ ያደረገህ ማን ነው? እኮ የጸጋ ልብስህን እንድታጣ ያደረገህ ማን ነው? ይህን የመሰለ ቅጽበታዊ መለወጥ ከወዴት መጣብህ? የከበረ ዕንቁህን እንድትጥል ያደረገህ ምን ቢገጥምህ ነው? አክብሮ በተወደደ ቦታ ካስቀመጠህና ኹል ጊዜ በስስት ዐይን ሲያነጋግርህ ከነበረው አምላክህ ተደብቀህ እንድትሸሸግ ያደረገህ ምንድነው? ማንም የወቀሰህ ሳይኖር፣ እንዲህ እንዲህ አድርገህ በድለሃል ብሎ የመሰከረብህ ሳይኖር ይህን ያህል በፍርሐት መናጥ ከወዴት አገኘህ?” ይላል /Daily Readings of St. John Chrysostom/።

ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ሆይ! ፮ ሺሕ ከ፮፪ ዘመን በግብርናተ ዲያብሎስ የነበረ አዳምን ነፃ ካደረገው ልጅሽ ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኝልን። “ቅድስት” ማለቱ ንጽሕት፣ ጽንዕት፣ ክብርት ልዩ ሲል ነው። ይኸውም፥-

- ሌሎች ሴቶች ከነቢብ ከገቢር ቢነጹ ከሐልዮ አይነጹም። እሷ ግን የዕንቆራው ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ቴዎዶጦስ “ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ ድንግል በሕሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ- ከፈጠራት ጀምሮ በምንም በምን (በሕሊናዋም በሥጋዋም) ከድንግልናዋ አልተለወጠችም” /ሃይ.አበ.፶፫፥፶፪/ እንዲል ከነቢብ፣ ከገቢር፣ ከሐልዮ ኃጢአት ንጽሕት ናትና።
- ጽንዕትም አለ። ሌሎች ሴቶች ቢጸኑ ለጊዜው ነው፤ ኋላ ተፈትሖ አለባቸው። እሷ ግን ቅድመ ፀኒስ ጊዜ ፀኒስ፤ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ ጽንዕት (ወትረ ድንግል) ናትና።
- ክብርትም አለ። ሌሎችን ሴቶች ብናከብቸው ጻድቃንን፣ ሰማዕታትን፣ ጳጳሳትን፣ ሊቃውንትን ወለዱ ብለን ነው። እሷን ግን ወላዲተ አምላክ ወልዳልናለች ብለን ነውና።
- ልዩም አለ። እናትነትን ከድንግልና፣ አገልጋይነትን ከእናትነት፣ ወተትን ከድንግልና ጋር አስተባብራ የተገኘች፤ በድንግልናም እያለች ከጡቶቿ ወተት ተገኝተው በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ የሚመግብ መጋቤ ፍጥረታት አምላክን የወለደች፤ እሳታውያን የሚኾኑ ኪሩቤል ሱራፌልም በፍርሐት በረዐድ ኾነው ዙፋኑን የሚሸከሙት እሳተ መለኮት ጌታን ፱ ወር ከ፮ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች፣ በክንዷ የታቀፈች፣ በዝርባዋ ያዘለች ከእመቤታችን በቀር ሌላ ሴት የለችምና።



“ለምኚልን” ሲልም ልክ በዚህ ምድር እንደነበረው ዓይነት ልመና ከዚያ በኋላ ኖሮባት አይደለም። ስንኳን በሷና በሌሎችም የለባቸውም። በቀደመ ልመናዋ የምታስምር ስለ ኾነ እንዲህ አለ እንጂ። ይኸውም በቃል ኪዳኗ ማለት ነው። አንድም በቁሙ ይተረጐማል። ማዘከር (ማሳሰብ) አለና።

“ሰአሊ ለነ ቅድስት” የሚለው ቅዱስ ኤፍሬም የተናገረው አይደለም። “ታድያ ይህን የጨመረው ማን ነው?” በሚለው ላይም ኹለት ዓይነት አመለካከለት አለ። “ቅዱስ ያሬድ ለዜማ መከፈያ ተናግሮታል” የሚሉ አሉ፤ “የኋላ ሊቃውንት ተናግረውታል” የሚሉም አሉ።

፪. ወዶም አልቀረም ዘር ምክንያት ሳይኾነው ከድንግል በሥጋ ተወለደ። “እኮ ወልደ ማርያም በመለኮቱ አላ በከመ ሥርዓተ ትሥብእቱ- በመለኮቱ የማርያም ልጅ አይደለም፤ በተዋሐደው ሥጋ ነው እንጂ” እንዲል ድርሳነ ቄርሎስ በመለኮት ሳይኾን በሥጋ ተወልዶ አዳነን።

ከእናንተ መካከል፡- “ልደቱ በዘርዕ ያላደረገው እንበለ ዘርዕ ያደረገው ስለ ምንድነው?” ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፡-

- አንደኛ፡ “ልደት ቀዳማዊ ተዐውቀ በደኃራዊ” እንዲል ፭ ሺሕ ከሯጀ ዘመን ሲፈጸም ከእመቤታችን ያለ አባት መወለዱ ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት እንደ ተወለደ ለማጠየቅ፤
- ኹለተኛ ደግሞ ሊቃውንቱ እንደሚነግሩን በዘርዕ በሩካቤ ተወልዶ ቢኾን ኖሮ መናፍቃን “ዕሩቅ ብእሲ ነው” ባሉት ነበርና ነው። ቅዱስ ጐርጐርዮስ ዘእንዚናዙ ይህን ሲያብራራው፡- “ሰውም በኾነ ጊዜ እንደ ዕሩቅ ብእሲ በዘር በሩካቤ አልተወለደም፤ አምላክ ሰው ኾነ እንጂ። እንደ ዕሩቅ ብእሲ በዘር በሩካቤ ተወልዶ ቢኾንስ ብዙ ሰዎች በተሳሳቱ ነበር፤ አምላክ ሰው መኾኑንም ሐሰት ባደረጉት ነበር” ይላል /ሃይ.አበው. ፷፡፲፱/። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም፡- “እንደ እኔስ በዘር በሩካቤ ተወልዶ ቢኾን ብዙ ሰዎች ዕሩቅ ብእሲ ባሉት ነበር፤ አምላክነቱንም በካዱት ነበር” ይላል /ሃይ.አበ. ፶፯፡፵፪/።

አሁንም ከእናንተ መካከል፡- “ያውስ ቢሆን ተፈትሐ ካላት ያላደረገው፣ ተፈትሐ ከሌላት ያደረገው ስለ ምንድነው?” ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፡-

- አንደኛ “እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች” ተብሎ የተነገረውን /ኢሳ.፯፡፲፬/ ለመፈጸም ሲኾን፤

- ኹለተኛው ደግሞ ምሳሌውን ለመፈጸም ነው። ይኸውም አዳም ከኅቱም ምድር ተገኝቷል /ዘፍ.፩፡፳፯/፤ ጌታም በኅቱም ማኅፀን ተወልዷል /ሕዝ.፵፬፡፩/። ሔዋን በኅቱም ገቦ (ጐን) ተገኝታለች /ዘፍ.፪፡፳፩/፤ ጌታም በኅቱም ማኅፀን ተወልዷል። ቤዛ ይሥሐቅ የሚኾን በግዕ ከኅቱም ጉንድ ተገኝቷል /ዘፍ.፳፪፡፲፫/፤ ቤዛ ዓለም ክርስቶስም በኅቱም ማኅፀን ተወልዷል። ጽምዐ እስራኤልን ያበረደ ውሃ ከኅቱም እብን (ዐለት) ተገኝቷል /ዘጸ.፲፯፡፯/፤ ጽምዐ ነፍሳትን ያበረደ ማየ ሕይወት ጌታም በኅቱም ማኅፀን ተገኝቷል። ጽምዐ ሶምሶንን ያበረደ ውሃ በኅቱም መንሰከ አድግ (የአህያ መንጋጋ) ተገኝቷል /መሳ.፲፭፡፲፱/፤ ጽምዐ ኃጥአንን ያበረደ ማየ ሕይወት ጌታም በኅቱም ማኅፀን ተገኝቷል። የዚህ ኹሉ ምሳሌ ፍጻሜው አንድ ነው። ይኸውም ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ 'ከመ ትኩን መራሒተ ለሃይማኖት ዐባይ - ለደገኛው ሃይማኖት መሪ ትኾን ዘንድ' /ሃይ.አበ.፰፯፡፴፪/ እንዲላት እመቤታችን ጌታን ብትወልደው ማኅተመ ደንግልናዋ እንዳልተለወጠ ኹሉ እርሱም ሰው ሲኾን አምላክነቱ ላለመለመጡ ምሳሌ ነው። ዳግመኛም እርሷ "ድንግል ወእም" ስትባል መኖሯ እርሱም "አምላክ ወሰብእ" ሲባል ለመኖሩ ምሣሌ ነው።

እናም አዳምን ያድነው ዘንድ የፈቀደ አምላክ ከይሲ ዲያብሎስ ያሳታት ሔዋንን "ጻርሽን ጋርሽን ምጥሽን አበዛዋለሁ" ብሎ እግዚአብሔር ከፈረደባት በኋላ ሊቁ አባ ሕርያቆስ "ፍቅር ሰሐቦ ለወልድ ኀያል እመንበሩ ወአብጽሖ እስከ ለሞት- የሰው ፍቅር ከዙፋኑ ስቦ ጐትቶ አወረደው፤ ከሞትም አደረሰው" እንዲል /ቅዳ.ማር. ቁ. ፻፳፭/ ሰውን ወደደና ሔዋንን ነጻ አደረጋት /ገላ.፭፡፩/። ሔዋንን ነጻ ካደረገ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፫. ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ አዳምን ነጻ ያደርገው (ያድነው) ዘንድ የፈቀደ፣ ሔዋንንም ወድዶ ነጻ ያደርጋት ዘንድ ሰው የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው /ዮሐ.፩፡፲፬/። ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለው ስም የመለኮት ብቻ ወይም የትስብእት ስም ብቻ አይደለም። "ወእነግር አነሂ ከመ ኢመፍትው እስምዮ ለቃለ እግዚአብሔር ክርስቶስ ዘእንበለ ትስእብት ወኢ ለትስብእት ዘእንበለ መለኮት ክርስቶስሀ ይሰመይ ወእም ቅድመ ትሥጉት አልቦ ዘይሰምዮ በዝንቱ ስም ለቃለ እግዚአብሔር ክርስቶስ- ክርስቶስ ሲል ብትሰማ ብቻ አምላክ እንደኾነ ብቻ ሰውም እንደኾነ አታስብ። አንድ እንደ መኾኑ ሰው የኾነ አምላክ ነው እንጂ" /ሃይ.አበ.፰፰፡፵/ እንዲል ከኹለት አካል አንድ አካል ከኹለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ቢኾን የወጣለት ስም ነው እንጂ።

አዳምን ነጻ ያደርገው ዘንድ ሰው የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ ላይ አደረ /ዮሐ.፩፡፲፬/። ለአባቱ እንደ አንድ ልጅ ክብር የሚኾን ክብሩንም አየንለት። ልጅ ለአባቱ አንድ የኾነ

እንደኾነ ደጃፍ የመለሰው ማጄት የጎረስው ኹሉ ገንዘቡ ነው። ለእርሱም "እስመ ኵሉ ዘቦ ለአቡየ ዚኣየ ውእቱ- ለአብ ያለው ኹሉ የእኔ ነው" /ዮሐ.፲፮፡፲፭/ እንዲል የአብ ገንዘብ ኹሉ ገንዘቡ ነውና ለአባቱ እንደ አንድ ልጅ የሚኾን ክብሩን አየንለት። "ወይሰገድ ከመዋሕድ- እንደ አባቱ ይመለካል" እንዲል ለአባቱ እንደ አንድ ልጅነቱ የሚኾን ክብሩን አየንለት። የአባቱን ጌትነት በደብረ ሲና እንዳየነ /ዘጸ.፲፱/ የእርሱንም ጌትነት በደብረ ታቦር አየንለት /ማቴ.፲፯፡፩-፰/። አባቱ በኤልያስ አድሮ አንድ ምዉት /፩ኛ ነገ.፲፯/፣ በኤልሳዕ አድሮ ኹለት ምዉት ሲያስነሣ እንዳየነው /፪ኛ ነገ. ፬/፤ እርሱም ሥጋን ተዋሕዶ የአራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን ሲያስነሣ አየነው /ዮሐ.፲፩/። ይህን ጠቅለል አድርጐ ቅዱስ ባስልዮስ ሲናገረው፡- "ስለ አብ የተናገርነው ኹሉ ለወልድ ገንዘቡ ነው። በመልክ ይመስለዋል፤ በባሕርይ ይተካከለዋልና። ወንጌላዊው ዮሐንስ ለአባቱ አንድ እንደ ኾነ ልጅ ክብር ያለ ክብሩን አየን አለ" ይላል /ዮሐ.፩፡፲፬፣ ሃይ.አበ.፴፫፡፳፰/።

የመጽሐፍ ልማድ ኾኖ የብሉዩን ለአብ የሐዲሱንም ለወልድ ሰጥቶ ተናገረ እንጂ ኹሉም በኹሉ አሉ። ከእናንተ መካከል፡- "ያውስ ቢኾን (ቅዱስ ኤፍሬም) ወዴት ነበርና ነው አየንለት የሚለው?" ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፡- አየንለት የሚለው የብሉዩን የእነ ሙሴን ዐይን ዐይን አድርጎ፤ የሐዲሱን ደግሞ የእነ ጴጥሮስን ዐይን ዐይን አድርጎ መናገሩ ነው። ይኸውም አባ ሕርያቆስ የሓዋርያትን መብል መብል አደርጎ፡- "በላዕነ ወሰተይነ ምስሌሁ - ከእርሱ ጋር በላን ጠጣን" እንዳለው ማለት ነው /ቅ.ማር. ቁ.፹፯/።

ይህ ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የኾነው ክብሩን ያየንለት ወዳጅ ይቅር ይለን ዘንድ ወደደ። ይቅር ይለን ዘንድ ከወደደ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና፤ እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፬. ነቢዩ ኢሳይያስ ትንቢት በሚገልጽ መንፈስ ቅዱስ የአማኑኤልን ምሥጢር አየና አሰምቶ ተናገረ። አማኑኤል ማለት ሰው የኾነ አምላክ ማለት ነውና "ሕፃን ተወለደልን፤ ወልድ ለሕማም ለሞት ተሰጠልን። አንድም ወልድ ለኩነተ ሥጋ ተሰጠልን ፤ ሕጻንም ኾኖ ተወለደልን" ብሎም ጮኸ /ኢሳ.፱፡፮/። አትናቴዎስ ሐዋርያዊም "ስለ ድኅነተ ሰብእ የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ፤ ካሣ ይከፍልልን ዘንድ ቃል ሥጋ ኾነ" ይላል /Ep. 61:3./። ወልድ ዘበላዕሉ ሕፃን ዘበታሕቱ ከሚባል ልጅሽ እመቤታችን ጽንዕት በድንግልና ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፭. ባሕርየ ዕጓለ እመሕያው (ሰው) ሆይ! እግዚአብሔር ሰውን ወዶታልና በውሰጥ በአፍአ፣ በነፍስ በሥጋ ደስ ይበልህ። "ወዶ ምን አደረገለት?" ትለኝ እንደኾነም "በእርሱ የሚያምን ኹሉ የዘላለም ሕይወት

እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" ተብሎ እንደተጻፈ /ዮሐ.፫፤፲፮/ ልጁን ለሕማም ለሞት እስከ መስጠት ደርሶ ለቤዛ ሰጥቶለታል ብዬ እመልስልሃለሁ። ልዑል እግዚአብሔር ረቂቅ ክንዱን ሰደደልን /ኢሳ.፶፩፥፱፣ ፶፫፥፩/። ነገር ግን ቅ.ዮሐንስ አፈወርቅ የዕብራውያንን መልእክት በተረጐመበተ በጀኛው ድርሳኑ "ወልድ ዋሕድ እንደ መላእክት በተላከ ጊዜ ቦታውን የለቀቀ አይደለም፤ በአንድ ፈቃድ ከአባቱ ጋር እያለ ነው እንጂ" ብሎ እንደተናገረው በለቢሠ ሥጋ ነው እንጂ በመለኮት የተላከ አይደለም። ክንድ ከአካል ሳይለይ የወደቀውን ዕቃ አንሥተው ይመልሱበታል፤ የራቀውንም ያቀርቡበታል። የአብ ኃይል፣ ክንድ የሚባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የወደቀውን አዳምን ያዳነው ከባሕርይ አባቱ፣ ከአባቱ አንድነት ሳይለይ ነው።

እዱ መዝራዕቱ ከሚባለው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኝልን።

፯. ሊቁ ምስጋናውን ሲቀጥል "እምቅድመ ዓለም የነበረው፣ ዓለምን አሳልፎ የሚኖረው፣ ለኩነት ሥጋ የመጣው፣ ዳግመኛም ዓለሙን ለማሳለፍ የሚመጣው አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ካንቺ ሳይለወጥ ፍጹም ሰው ኾነ" ይላል። ይኸውም በሌላ አንቀጽ "ባሕርዩን ከፍሎ አልተዋሐደምና፤ ባሕርዩንም ሕፀፅ በማድረግ ኹለተኛ እንስሳ አልኾነም። አንድ አካል አንድ ባሕርይ በመኾን ምሉ ፍጹም ሰው ነው እንጂ። የአምላክነትን የሰውነትንም ሥራ ይሠራልና፤ ይህስ ባይኾን አንዱ ተለይቶ በቀረ ነበር" ካለው ጋር ተመሳሳይ ነው /ዮሐ.፩፥፩-፲፬፣ ሃይ.አበ.ዘኤፍሬም ፵፯፥፵፪/።

"ተቀዳሙ ተከታይ የሌለው ወልድ ዋሕድ በሥራው ኹሉ ከነሣው ሥጋ አልተለየም።" ይህም በኹለት መልኩ ይተረጐማል፡-

፩ኛ፡- "አካላዊ ቃል አንድ ግብር፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ አካል ነው እንጂ" ማለት ሲኾን፤

፪ኛ፡- ደግሞ "ተቀዳሙ ተከታይ የሌለው ወልድ ዋሕድ ሰውም ቢኾን ከአብ ከባሕርይ አባቱ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ አልተለየም። አካላዊ ቃል አንድ ጎብረ መልክዕ፣ አንድ ባሕርይ፣ አንድ አገዛዝ ነው እንጂ" ማለት ነው።

ሰውም ቢኾን ከአብ ከባሕርይ አባቱ፣ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ ካልተለየ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳነሣን ለምኝል።

፯. ዳግማይ አዳም (ክርስቶስ) ካንቺ ባንቺ ባሕርይ ተወልዷልና የነቢያት ሀገረ ትንቢታቸው ቤተ ጎብስት እመቤታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ። የቀደመ ሰው አዳምን ከሲዖል ወደ ገነት ከጎሣር ወደ ክብር ይመልሰው ዘንድ ካንቺ ባንቺ ባሕርይ ተወልዷልና የነቢያት ሀገረ ትንቢታቸው ቤተ ጎብስት እመቤታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ። ከእናንተ መካከል፡- "ሊቁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዳግማይ አዳም ማለቱ ከቀዳማዊ አዳም ጋር

የሚያመሳስለው ምን ስላለው ነው?" ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፡- በቀዳማዊ አዳም ምክንያት የሰው ልጅ በሙሉ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም ተፈርዶበት ነበር፤ በዳግማይ አዳም በክርስቶስ ግን የጽድቅ በር ለኹሉም ተከፍቷል። ከቀዳማዊ አዳም ጋር አብረው ዕፀ በለስን ያልበሉት ስንኳ ሞት ነግሦባቸው ይኖር ነበር፤ በዳግማይ አዳም በክርስቶስ ትሩፋት ግን የሰው ልጅ በሙሉ የድኅነት መንገድ ተሰጥቶታል። ስለዚህ ክርስቶስ ዳግማይ አዳም ሲባል በአዳም የመጣው በደል ክርስቶስ ከሰጠው ጸጋ ጋር ወይም ደግሞ በአዳም ምክንያት የመጣው ሞትና በክርስቶስ የተሰጠው ሕይወት ለማስተካከል ሳይኾን አዳም ለሚሞቱት ኹሉ አባት እንደኾነ ኹሉ ክርስቶስ ደግሞ ትንሣኤ ሕይወት ላላቸው ኹሉ አባታቸው መኾኑን ለመግለጥ ነው /St. John Chrysostom on Romans, Hom.10/። አንድም በጥንተ ተፈጥሮ ይመስሏልና።

በዕፀ ምክንያት የወደቀ (ከገነት የወጣ፣ ከክብሩ የተዋረደ) አዳም ንስሐ ቢገባም፣ ጩኸቱን ሰምተው ነቢያት ካህናት ቢነሡም እንደ እርሱ ንጽሐ ጠባይዕ አድፎባቸዋልና በግዘረታቸው በመሥዋዕታቸው አዳምን ማዳን አልቻሉም /ኢሳ.፷፬፡፮/። ነገር ግን "አንሥእ ኃይለከ፤ ፈኑ እዴከ" /ኢሳ.፶፩፡፱/ ያሉትን ልመናቸውን ሰምቶ ካንቺ ባንቺ ባሕርይ ተወለደ (ሰው ኾነ)። የአዳምን ባሕርይ ባሕርይ አድርጐ "አዳም ጥንቱንም መሬት ነህ ወደ መሬትነትህ ተመለስ" ብሎ በአዳም የፈረደበትንም የሞት ፍርድ (መከራ) ተቀብሎ ያድነው ዘንድ ካንቺ ባንቺ ባሕርይ ተወልዷልና፣ የነቢያት ሀገረ ትንቢታቸው ቤተ ጎብስት እመቤታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ። ብዙ ኃጢአት ካለች ዘንድ ጸጋ እግዚአብሔር ትበዛለች /ሮሜ.፭፡፳/። "በአንድ ሰው (አዳም) ምክንያት የገባች ኃጢአት ሕግ በተሰጣቸውና ባልተሰጣቸው ኹሉ እንዲህ ከነገሠች፣ በዳግማይ አዳም በአካላዊ ቃል በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠች ጸጋማ እንዴት አብልጣ አትበዛ?" /St. John Chrysostom, Ibid/። **ዳግማይ አዳም ከሚባል ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳነሣን ለምኚልን።**

፰. የሰው ኹሉ አእምሮ በአፍአ በውስጥ በሥጋ በነፍስ ደስ ይላታል። "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ- አምላክ ለኾነ ለሥጋ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ በአንድነት ምስጋና ይገባዋል። በምድርም ዕርቅ ተወጠነ። የሰው ግዕዛኑ ይሰጠው ዘንድ" እያሉ ከመላእክት ጋራ (እንደ መላእክት) ንጉሥ ክርስቶስን ያመሰግኑታል /ሉቃ.፪፡፲፬/። አንድም "ዮም አሐደ መርዓት ኮኑ መላእክት ወሰብእ ከመ ይሰብሕዎ ለክርስቶስ በቃለ አሚን- " እንዲል የሰው ፍቅር አገብሮት አምላክ ሰው ቢኾን ሰውም አምላክ ቢኾን በመላእክት ዘንድ ምስጋና ተደረገ። በምድርም አንድነት ተደረገ፤ ኖሎት (እረኞች) ከመላእክት ጋራ አንድ ኾነው አመሰገኑ /ሉቃ.፪፡፳/። "ኃጢአትን አጠፋ፤ በመስቀልም ተሰቅሎ ፍዳን አጠፋ። በመቃብርም ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አጠፋ። በሲዖልም ሞተ ነፍስን አጠፋ። ሥራ በሠራበት ኹሉ ድኅነትን አደረገልን" እንዲል የቀደመ መርገመ ሥጋ መረገመ ነፍስን አጥፍቷልና ኖሎት ከመላእክት ጋራ

አንድ ኾነው አመሰገኑ /ሃይ.አበ.፹፱፡፳፱/። የጸላኢ የዲያብሎስ ምክሩን አፍርሶበታልና ኖሎት ከመላእክት ጋራ አንድ ኾነው አመሰገኑ። በመቅድመ ወንጌል "ወበከመ ኮነ በጉህለት ተጎብአ ሰይጣን ውስተ ሥጋ ከይሲ ከማሁ ኮነ ድኅነትነ በተሰውሮ ቃለ እግዚአብሔር ዘመድኃ- ሰይጣን በተንኰል በሥጋ ከይሲ እንደተሠወረ እኛም ከፍዳ መዳናችን ቃለ እግዚአብሔር በባሕርያችን በመሠወሩ ኾነ" እንዲል በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ ቢያስትበት በሥጋ ተሰውሮ አድኖበታልና ኖሎት ከመላእክት ጋራ አንድ ኾነው አመሰገኑ። ዲያብሎስ "ሥጋን በመቃብር ነፍስን በሲኦል ተቆራኝቼ እኖራለሁ" ብሎ ነበርና የመከረባቸውን ሥጋንና ነፍስን ተዋሕዶ አድኖበታልና ኖሎት ከመላእክት ጋራ አንድ ኾነው ንጉሥ ክርስቶስን አመሰገኑ። ይኸውም ጥበበኛው ሰሎሞን "ጠቢብ የኃያላንን ከተማ ይገባባታል፥ የሚታመኑበትንም ኃይል ያፈርሳል" እንዳለው ነው /ምሳ.፳፩፡፳፪/።

ይህም ብቻ አይደለም፤ የአዳምንና የሔዋንን የዕዳ ደብዳቤቸውን አጥፍቶላቸዋልና /ቈላ.፪፡፲፬/ "አምላክ ለኾነ ለሥጋ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ በአንድነት ምስጋና ይገባዋል። በምድርም ዕርቅ ተወጠነ። የሰው ግዕዛኑ ይሰጠው ዘንድ" እያሉ መላእክት አመሰገኑት /ሉቃ.፪፡፲፬/። ዲያብሎስ በአዳምና በሔዋን የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ ሥቃይ አጽንቶ "ስመ ግብርናት ጽፍችሁ ብትሰጡኝ አቀልላችኋለሁ" ብሏቸው አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ ሔዋንም አመቱ በዲያብሎስ ብለው ጽፈው ሰጥተውት ነበር። ዲያብሎስም ያንን በእብነ ሩካም ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ አንዱን በሲኦል ጥሎት ነበር። አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖ ሲመጣ ግን ዲያብሎስ በዮርዳኖስ የጣለውን ሲጠመቅ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ እንደ ሰውነቱ ተረግጦ አጥፍቶታል፤ በሲኦል የጣለውንም በዕለተ ዐርብ በአካለ ነፍስ ወርዶ አጥፍቶላቸውና መላእክት አመሰገኑት /ቈላ.፪፡፲፬/። በዳዊት ሀገር ከዳዊት ባሕርይ የተወለደ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳምና ሔዋንን ነጻ አድርጓቸዋልና አመሰገኑት /መዝ.፻፴፪፡፲፯/። አዳምንና ሔዋንን ነጻ ካደረጋቸው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፱. በዚህ ዓለም ለሚኖሩ ሰዎች ኹሉ የምታበራ (ዕውቀትን የምትገልጥ)፣ ጠፈር ደፈር የማይከለክልህ፣ መዓልትና ሌሊትም የማይፈራረቅብህ ብርሃን ዘበአማን (እውነተኛ ብርሃን) ክርስቶስ ሆይ! ስለ ሰው ፍቅር ልሙት ልሰቀል ብለህ ወደ ዓለም በመምጣትህ ፍጥረት ኹሉ ደስ አለው። አዳምን ከስሕተት፣ ሔዋንንም ከሞት ፃዕረኝነት (ከመጣባቸው ፍዳ) ነፃ አድረገኻቸዋልና ለእኛ በተደረገው ክብር መላእክት ከእኛ ጋር ደስ አላቸው /ሃይ.አበ.፷፯፡፴፪/። የሰው ፍቅር አገብሮህ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስነህ ሲያዩህ "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር" ብለው መላእክት አመሰገኑ። ከዚህም የተነሣ በጣዕም ላይ ጣዕም በጸጋ ላይ ጸጋ ተጨምሮላቸው ደስ ብሏቸዋል። እኛም ቅብዐ ትፍስሕት የሚኾን መንፈስ ቅዱስን

አንድም ሀብተ ልደትን ተቀብለን ከመላእክት ጋር ደስ አለን፤ አመሰገንንህም። እንስሳት፣ አራዊት ስንኳ ሳይቀሩ ሰው ከፈጣሪው ጋር በመታረቁ ደስ ብሏቸዋል።

ጽንዕት በድንግልና ቅድስት እመቤታችን ሆይ! ብርሃን ከሚባል ልጅሽ ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

ይህንን ሲጨርስ በያዘችው መስቀለ ብርሃን ባርካው ዐረገች፤ እርሱም እጅ ነሥቶ ቀርቷል።

አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮም ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

የማክሰኞ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ

ገ/እግዚአብሔር ኪደ

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ ነሐሴ ፮ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም)፡- ለምስጋና ዅለተኛ፣ ለፍጥረት ሦስተኛ ቀን በሚኾን በዚህ ቀንም እመቤታችን ትመጣለች፤ የብርሃን ድባብ ይዘረጋል፤ የብርሃን ምንጻፍ ይነጸፋል። ከዚያ ላይ ኾናም፡- "ሰላም ለከ ኦ ፍቁርየ ኤፍሬም" ትለዋለች። እርሱም ታጥቆ እጅ ነሥቶ ይቆማል። ክርክር በዕለተ ሰኑይ አልቋልና "ባርክኒ" ብሎ ተባርኮ "አክሊለ ምክሕነ" ብሎ ምስጋናውን ይጀምራል።

፩. ዳዊት ምንም ንጉሠ ነገሥት ቢባል የመመኪያችንን ዘውድ ማምጣት አልተቻለውም /፩ኛ ሳሙ.፲፮፡ ፲፫/። ኢያሱ ምንም የስሙ ትርጓሜ መድኃኒት ቢኾንም የደኅንነታችን መጀመሪያ መኾን አልተቻለውም። ኤልያስም ምንም ንጹሕ፣ ድንግል ቢኾንም የንጽሕናችን መሠረት መኾን አልተቻለውም። የመመኪያችን ዘውድ፣ የደኅንነታችን መጀመሪያ፣ የንጽሕናችን መሠረት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የመመኪያችን ዘውድ "አክሊለ ሰማዕት" የሚባል ጌታችን ነው። የደኅንነታችን መጀመርያ "ጥንተ ሕይወት" የሚባል ጌታችን ነው። የንጽሕናችን መጀመርያም ዅሉ በእጁ የተጨበጠ፣ ዓለምንም በመዳፉ የያዘ፤ በጠፈር ላይ የሚቀመጥ ፣ ዳግመኛም መሠረቱን ከታች የሚሸከም "መሠረተ ዓለም" የሚባል ጌታችን ነው /ቅዳ.ማር. ቁ.፶፭/። እርሱም አካላዊ ቃልን በወለደችልን በድንግል ማርያም ተገኝልን። እኛን ስለማዳን ሰው ኾነ፤ ሰውም ከኾነ በኋላ ግን ፍጹም አምላክ ነው። ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ እንደ ወለደችው ዅሉ እርሱም አምላክነቱ ሳይለወጥ ሰው ኾነ። እርሷ "ድንግል ወእም (ድንግልም እናትም)" ስትባል እንደምትኖር ዅሉ እርሱም "አምላክ ወሰብእ (ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው)" ሲባል ይኖራል /ሃይ.አበ.፷፯፡፯/። ተፈትሖ ሳያገኛት (ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ) እንደምን እንደወለደችው ግን የማይመረመር አንድም ሊነገር

የማይችል፣ ከኀሊናት ኹሉ የሚያልፍ ድንቅ ነው። በማይመረመር ግብር ከወለድሽው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፪. “ቃል ሥጋ ኾነ” እንዲል በእርሱ ፈቃድ /ዮሐ.፩፡፲፬/፣ “ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና” እንዲል በአባቱ ፈቃድ /ዮሐ.፫፡፲፮/፣ “በመንፈስ ቅዱስ በኀይልም እንደ ቀባው” እንዲልም /ሐዋ.፲፡፴፰/ በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሰው ኾኖ አዳነን። ሊቁ እንዲህ ማለቱ “ወልድ ያለ ፈቃዱ ሰው ኾነ” የሚሉ መናፍቃን ስላሉ ነው። ሌሎች ሊቃውንትም፡- “የእግዚአብሔር ልጅ ያለ ፈቃዱ ሰው እንደ ኾነ የሚያምን፤ የሚያስተምር፤ ወይም የአብ ፈቃድ ሌላ ነው፤ የወልድ ፈቃድ ሌላ ነው፤ የመንፈስ ቅዱስም ፈቃድ ሌላ ነው የሚል ቢኖር፤ ፈቃዳቸው አንድ፤ መንግሥታቸውም አንድ እንደኾነ የማያምን ሰው ቢኖር ውጉዝ ይኹን” ብለው አስተምረዋል /ሃይ.አበ.፶፭፫፪/።

በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ፍጽምት የምትኾኚ እመቤታችን ሆይ! በድንግልና ጸንተሽ ብትገኚ ላንቺ የተሰጠሽ ጸጋ ፍጹም ነው። እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ካንቺ ጋራ አንድ ባሕርይ ቢኾን አንድም በጸጋ ቢያድርብሽ ባለሚልነትን አግኝተሽልና ለአንቺ የተሰጠ ክብር ፍጹም ነው። ይህ ከቃላት በላይ የሚያልፈው ባለሚልነቷ ቅዱስ ባስልዮስ ከሌሎች ቅዱሳን ጋር እያነጻጸረ ሲያብራራው፡- “የዚህ ዓለም ነገር ኹሉ አይመጥናትምና የሚመጥናትን ምን ዓይነት ምስጋና እናቅርብላት? ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ቅዱሳን ሲናገር ዓለም አልተገባቸውም /ዕብ.፲፩፡፴፰/ ካላቸው ከከዋክብት በላይ ኾና እንደምታበራው ፀሐይ ለኾነችው ለአምላክ እናትማ ምን ልንል እንችል ይኾን?... ምን ምሥጢር እንደተከናወነ ተመልከት፤ ኀሊናን አእምሮን የሚያልፍ ነገር እንደኾነም አስተውል። ታድያ የአምላክ እናት ታላቅነት እንደምን ኹሉም ሰው አይናገር? ማንስ ነው ከቅዱሳን ኹሉ በላይ እንደኾነች ያላስተዋለ? እግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ የሚልቅ ጸጋን ከሰጠና የሚነኩት ኹሉ ሰው ከበሽታው ከተፈወሰ፣ ጥላቸው ያረፈበት ተአምር ከተፈጸመለት፣ ጴጥሮስ በጥላው ካዳነ /ሐዋ.፭፡፲፭/፣ የጳውሎስ የልብሱ ዕራፊ መናፍስትን ካወጣ /ሐዋ.፲፱፡፲፭/ ለእናቱማ ምን ዐይነት ሥልጣንና ኀይል ተሰጥቷት ይኾን? በምን ዓይነትስ ሥጦታ አስጊጧት ይኾን? ጴጥሮስ፡- ክርስቶስ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ስላለው ብፁዕ ነህ ከተባለና የመንግሥት ሰማያት ቁልፍ ከተሰጠው /ማቴ.፲፮፡፲፮-፲፱/ እርሷማ ከኹሉም ይልቅ እንዴት ብፅዕት አትኾን? /ሉቃ.፩፡፵፭/ ጳውሎስ ታላቅ ክብር ያለውን የክርስቶስን ስም በመሸከሙ ምርጥ ዕቃ ከተባለ /ሐዋ.፱፡፲፭/ የአምላክ እናትማ የምእመናን ምግብ የኾነ መናውን ሳይኾን የሕይወት ሰማያዊ እንጀራን ያስገኘች እርሷ ምን ዓይነት ልዩ ዕቃ ትኾን? ... ነገር ግን ስለ እርሷ ብዙ

እናገራለሁ ብዬ ስለ ክብሯ ጥቂት በመናገር ራሴን በጎፍረት ውስጥ እንዳልጨምር እፈራለኑ። ስለዚህ ከአሁን ወዲህ የንግግሬን መልሕቅ ስቤ በዝምታ ወደቤ ላይ ማረፍን መርጫለሁ" ይላል /መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ፣ ነገረ ማርያም በሐዲስ ኪዳን፣ ገጽ ፯-፶፩ ይመልከቱ/።





ከምድር እስከ ሰማይ ደርሳ፣ በላይዋ ዙፋን ተነጽፎባት በዚያ ላይ ንጉሥ ተቀምጦባት፣ መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ያያት የወርቅ መሰላል አንቺ ነሽ /ዘፍ.፳፰፡፲፰-፲፱/። መተርጕማኑ ይህ ምን ማለት እንደኾነ ሲያብራሩ፡- "ከምድር እስከ ሰማይ መድረሷ የልዕልናዋ፣ በላይዋ ላይ ዙፋን ተነጽፎባት ንጉሥም ተቀምጦባት ማየቱ ፱ ወር ከ፮ ቀን በማኅፀኗ ለመሸከሟ፣ መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ማየቱ ደግሞ ጌታችን ከእመቤታችን ሰው ከመኾኑ አስቀድሞ ሰው የጸለየውን ጸሎት ያቀረበውን መሥዋዕት ለማሳረግ አይወጡም አይወርዱም ነበር፤ ጌታችን ከእመቤታችን ሰው ከኾነ በኋላ ግን ለተልእኮ የሚወጡ የሚወርዱ ኾነዋልና ሲል ነው" ይላሉ /ሉቃ.፪፡፲፬፣ ሐዋ.፲፫-፲፣ የኦሪት ዘልደትን ትርጓሜ ይመልከቱ/። ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ በአምሳለ ንጉሥ ካየው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፫. ነደ እሳት ሰፍሮባት፤ በነደ እሳት ተከባ (ጫፎቿ) ሳትቃጠል ሙሴ በደብረ ሲና ያያት ዕፅ አንቺ ነሽ /ዘጸ.፫፥፫-፫/። ነደ እሳትም ያልኹት ሰው ኾኖ በማኅፀንሽ ፱ ወር ከ፯ ቀን ያደረው ወልደ እግዚአብሔር ነው። ምንም እንኳን አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ቢኾንም እሳተ መለኮቱ አላቃጠለሽም። አባ ሕርያቆስ ይህ ከኅሊናት የሚያልፈውን ነገር ሲያደንቅ ፡- “ቅድስት ድንግልን ለኹሉ ድንቅ የሚኾን የፅንሷን ነገር እንዲህ እያልን እንመርምራት። ድንግል ሆይ! እሳተ መለኮት በማኅፀንሽ ባደረ ጊዜ አካሉ እሳት ነው፤ መጐናጸፍያው እሳት ነው፤ ቀሚሱ መቋረፍያው እሳት ነው። እንደምን አላቃጠለሽ? ብለን እንመርምር። ሰባት የእሳት ነበልባል መጋረጃ በማኅፀንሽ ወዴት ተዘጋጀ? ወዴት ተጋረደ? በቀኝ ጐንሽ ነውን? ወይስ በግራ ጐንሽ ነውን? ሦስት ክንድ ከስንዝር ቁመት የተወሰንሽ ስትኾኚ እንደምን ቻልሽው? የአሥራ አምስት ዓመት ቆንጆ ስትኾኚ አንበሩ ሻኩራው ነደ እሳት የሚኾን፤ ዐይን የሚበዘብዝ ኪሩቤል የተሸከሙት መንበር ወዴት ተዘረጋ? ወዴት ቆመ?” ይልና /ቅዳ.ማር.ቁ.፩፯-፩፰/ “ኅሊናዬ ይህን አልመረምርም ብሎት ወደ ቀደመ አኗኗሩ ይመለሳል” ብሎ ይቋጨዋል /ቁ.፹፱/።

ሙሴ ያየው ሐመልማል ነበልባሉን እንዳላጠፋው ኹሉ ጌታም ምንም እንኳን ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽም ነፍስ ነሥቶ ቢዋሐድም ባሕርየ መለኮቱ አልተለወጠምና ሙሴ በደብረ ሲና ያያት ዕፅ አንቺ ነሽ ። ሙሴ በአምሳለ ሐመልማል ወነበልባል ካየው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፬. አንቲ ውእቱ ገራኅተ ዘኢተዘርዐ ውስቴታ ዘርዕ - ዘር ያልወደቀባት፣ ገበሬ ያልጣረባት ያልጋረባት፣ ለታብቁል (ታብቅል) ባለው ቃል ብቻ ከልምላሜ፣ ከጽጌ (ከአበባ)፣ ከፍሬ የተገኘች ገራኅተ ሠሉስ (የማክሰኞ እርሻ) አንቺ ነሽ። የወንድ ዘር ሳይወድቅብሽ ፍሬ ሕይወት (የሕይወት መገኛ) ጌታ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ካንቺ ተወልዷልና። አረጋዊው ዮሴፍ በትሩፋተ ደሙ የዋጀሽ /ቅዳ.ማር. ቁ. ፱፯፭/፣ ዕንቁ የተባለው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስንም ያገኘብሽ /ሃይ.አበ.፯፯፥፶፭/ የተቈለፈች ሣጥን አንቺ ነሽ። በዚህ አለ፣ በዚያ የለም የማይሉት ሙሉዕ በኩለሄ የኾነ አካላዊ ቃል በማኅፀንሽ አደረ /መዝ.፻፴፬፥፭/፤ በዚህ ዓለምም ማኅተመ ድንግልናሽ እንደተቈለፈ ወለድሽው /ሕዝ.፵፬፥፩-፪/። በዕንቁ ከተመሰለው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፭. ሥጋዌውን ተልከው ለነቢያት ሲነግሩ የነበሩ፣ አሁን ደግሞ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ

አይተውት “ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር” ብለው በደስታ ያመሰገኑትን ጌታን የወለድሽው ሆይ! ደስ ይበልሽ።

የነቢያት ዜና ትንቢታቸው ንጽሕት ሆይ! ደስ ይበልሽ። አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው፡- “ኦ ድንግል አምሳል ወትነቢት ዘነቢያት- ነቢያት ትንቢት የተናገሩልሽ ምሳሌ የመሰሉልሽ...” ይላታል /ቅ.ማር.ቁ.፹፯/። እግዚአብሔር ከነፍስሽ ነፍስ ከሥጋሽ ሥጋ ነሥቶ ካንቺ ጋራ አንድ ባሕርይ ኾኗልና ደስ ይበልሽ። አንድም እግዚአብሔር በጸጋ ቢያድርብሽ ባለሟልነትን አግኝተሻልና ደስ ይበልሽ። የሰው ዅሉ ደስታ የሚኾን የመልአኩን ቃል እንደ ኒቆዲሞስ ሳትከራከሪ /ዮሐ.፫፡፩-፱/ እንደ ዘካርያስም ሳትጠራጠሪ /ሉቃ.፩፡፳/ አምነሻልና ደስ ይበልሽ /ሉቃ.፩፡፵፭/። ሃያውን ዓለም የፈጠረ ጌታ የወለድሽው ሆይ! ደስ ይበልሽ።ሃያውን ዓለም ከፈጠረ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳያሣጣን ለምኝልን።

፯. በእውነት ወላዲተ አምላክ ተብለሻልና ደስ ይበልሽ። አንድም በሚገባ ወላዲተ አምላክ ተብለሻልና ደስ ይበልሽ። አንድም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፡- “ብልህ ሸክላ ሠሪ የሚሠራውን የለዘበ ጭቃ በአገኘ ጊዜ ከእርሱ መልካም ዕቃ እንዲሠራ፤ እንደዚህም ጌታችን የዚህችን ድንግል ንጹሕ ሥጋዋን ንጽሕት ነፍሷን ባገኘ ጊዜ ነፍስ ያለችውን ሥጋ ሊዋሐደው ፈጠረ” /ሃይ.አበ.፷፯፡፲፱/ እንዲል በቅተሽ ብትገኚ ወላዲተ አምላክ ተብለሻልና ደስ ይበልሽ።

የሔዋን ደኅንነቷ ሆይ! ደስ ይበለሽ። ሊቁ ያዕቆብ ዘሥሩግም እንዲህ ይላል፡- “የሕዝቦች ሴቶች ልጆች ሆይ! ከአባቶቻችሁ ስሕተት ነጻ ያወጣችሁን ቅረቡትና፤ እርሱንም ማመስገን ተማሩ። ያ ሔዋን የዘጋችውን የማይናገር አፍ አሁን በእመቤታችን ማርያም ተከፍቷልና ለእጎታችሁ ምስጋናን ለመዘመር ቅረቡ። አሮጊቷ ሴት (ሔዋን) በምላሶቻችሁ ዙርያ የዝምታን ገመድ ቋጠረችና፤ የድንግል ልጅ ግን ጮኻችሁ ታመሰግኑ ዘንድ እሥራታችሁን ፈታ...” /A Metrical Homily on Holy Ephrem, pp 47/። ከአባቶች አንዱም፡- “እንግዲህስ ሴቶች ዅሉ ሐሴት ያድርጉ፤ አሁን ሴቲቱ ዕፀ በለስን ሳይኾን ዕፀ ሕይወትን አስገኝታለችና። ዳግመኛም ደናግላን እናቶች ዅሉ በፈሽታ ይዝለሉ፤ ያለመታዘዝን ዕፅ በሴት ተፈውሷልና። እነሆ ክብሩ ከመላእክት ይልቅ የከበረ ኾኗልና ከእንግዲህ ወዲህ የሴትነት ጸታ የሞትና የውድቀት ምልክት መኾኑ ቀርቷል። ሔዋን ተፈወሰች፤ ድንግል ግን ከበረች። እነሆ ድንግሊቱ እናትም አገልጋይም፣ ደመናም ድንኳንም፣ ደግሞም የጌታ ታቦት ኾናለችና። እንግዲያውስ ኑ! አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ

ነሽ፤ የሔዋን መድኃኒቷ አንቺ ብቻ ነሽ፤ ዓለምን በደሙ የሚገዛትን ጌታ ያስገኘሽ አንቺ ብቻ ነሽ እያልን እናወድሳት" ብሏል።

ፍጥረትን ኹሉ በፀሐይ አብስሎ በዝናብም አብቅሎ የሚመግበውን እርሱ ጡትሽን ይዘሽ አጥተሸዋልና ደስ ይበልሽ። አንድም ለመንፈሳውያን ኹሉ ሥጋውን ደሙን ሰጥቶ የሚመግበውን እርሱን ጡትሽን ይዘሽ አጥብተሸዋልና ደስ ይበልሽ።

ተጠምቀው ሕያዋን ኾነው የሚኖሩበት ማየ ገቦ ከአንቺ ከተገኘ ከጌታ የተገኘ ነውና የሕያዋን የጻድቃን እናታቸው ንእድ ክብርት ሆይ! ደስ ይበልሽ። መቅድመ ተአምርም፡- "ሕይወትየ ይቤላ አዳም ለብእሲቱ አእሚሮ ከመ ትወጽእ እግዝእትነ ማርያም እምሐቄሁ ወእምከርሠ ብእሲቱ - አዳምም እመቤታችን ማርያም ከሱ አብራክ እንድትከፈል ከሔዋንም ማኅፀን እንድትወለድ ዐውቆ ሔዋንን ሕይወቴ ነሽ ይላት ነበር" ይላል /መቅድመ ተአምር ቁ. ፲/። ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግም፡- "አዳም ያለ ሩካቤ ድንግል የኾነች ሔዋንን አስገኘ፤ የሕይወት እናት ብሎም ጠራት። በዚህም ነቢይ ኾነ፤ በኹለተኛ ልደት ከእርሷ የሚያበራ ሕይወት ይገለጣልና፤ በድንግልናዋም የእግዚአብሔር ልጅን ታስገኛለችና። በአዳም ትንቢት የእውነት ሕይወት የኾነው የጌታችንን መምጣት በምሳሌ ተናገረ። እናቱም ድንግል ማርያም ኾነች። ሔዋንን የሕያዋን ኹሉ እናት ብሎ ጠራት፤ ሕይወትን አስገኝታለችና። እርሱም ኢየሱስ የተባለው ጌታችን ነው" ይላል /Jacob of Serug, On the Virgin, pp 36/። አንድም "ነዋ ወልድኪ- እነሆ ልጅሽ" /ዮሐ.፲፱፡፳፮/ ባለ ጊዜ በዮሐንስ እኛን ለእርሷ መስጠቱ ነውና የሕያዋን ኹሉ እናታቸው ንዕድ ክብርት ሆይ! ደስ ይበልሽ። ለምኚልንና ትልምኝልን ዘንድ ዓይነ ሕሊናችንን ወደ አንቺ እንሰቅላለን።

፯. ድንግል ሆይ! ንዕድ ክብርት ሆይ! ጌታን የወለድሽው ሆይ! እኛን ለማዳን ድንቅ የሚያሰኝ ተዋሕዶ በአንቺ ቢደረግ ንጉሥን ወለድሽልን፤ መንክር በአርያሙ የሚባል ጌታ በማኅፀንሽ አደረ። ነገር ግን በብዙ ኅብረ መልክእ፣ በብዙ ዖታ መልክእ ሃያ ኹለቱን ሥነ ፍጥረት የፈጠረ፣ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን በብዙ ዖታ በብዙ ዕድል እንደየ ሰዉ የአእምሮ ስፋት የሃይማኖት ጽናት የሚያድል፣ ልዕልናውን ገናንነቱን በብዙ መንክር ራዕይ በብዙ ወገን (ለምሳሌ በፀሐይ፣ በቀላይ፣ ...) የተመሰለ እርሱን የጌትነቱን ነገር ጠንቅቀን (ፈጽመን) መናገር አይቻለንምና ዝም እንበል። ዳግመኛም በብዙ ኅብረ ትንቢት (ለምሳሌ ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ ተብሎ) የተነገረ፣ በብዙ ኅብረ አምሳል (ለምሳሌ በአምሳለ ነበልባል ወሐመልማል፣ በአምሳለ ጠል ወፀምር፣

በአምሳለ አንበሳ፣ በአምሳለ እብን ቅውም) የተመሰለ የርሱን የሥጋዊውን ነገር ጠንቅቀን (ፈጽመን) መናገር አይቻለንምና ናርምም (ዝም እንበል)።

ሥጋዊው በአምሳለ ነበልባል ወሐመልማል፣ በአምሳለ ጠል ወፀምር ከተመሰለ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፯. ወደ ደብረ ሲና የወረደው፣ ለሙሴ ሕገ ኦሪትን የሠራ፣ የተራራውን ራስ በጨለማ በእሳት በጽጋግ በነፋስ (በዕበየ ግርማው) የሸፈነ፣ ፈርተው የቆሙትን ፈጥኖ ፈጥኖ በሚሰማ በረቂቅ ነጋሪት ድምጽ የገሠፀ እርሱ የሰው ልጆችን ለማዳን ፮ ሺሕ ፮፻ ዘመን ሲፈጸም ሰው ኾኖ የመጣው የአብ አካላዊ ቃል ነው። በሌላ አንቀጽም ይኸው ሊቅ፡- "እም ደብረ ሲና ወፅአ እሳት ወጽልመት ወእምኔኪ ወፅአ ለነ አምላክ ወሰብእ። እም ደብረ ሲና ወፅአ ድንጋፄ ወሀውከ ላዕለ አይሁድ ወእምኔኪ ወፅአ ሁከት ወድንጋፄ ዐቢይ ላዕለ አይሁድ ወሄሮድስ ወዲያብሎስ ምስለ አጋንንቲሁ - ከደብረ ሲና እሳት ጨለማ ወጣ፤ ከአንቺ ግን ሰው የኾነ አምላክ ተገኝልን። በደብረ ሲና በአይሁድ ላይ ድንጋፄ ሀውክ ተደረገ፤ በአንቺም በአይሁድ በሄሮድስ በዲያብሎስና በሠራዊቱ ላይ ጽኑ ድንጋፄ ተደረገ" ብሏል /ዘጸ.፳፡፲፰፣ ዕብ.፲፪፡፲፱፣ ሃይ.አበ.፵፯፡፱-፲/። እንዲህ ከተባለ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፰. "ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ" ከሚለው የኢሳይያስ አንቀጽ /ኢሳ.፯፡፲፬/ ስትደርሺ "እኔ በኾንኩኝ" ሳትዪ፤ ይልቁንም "ምነው ከዘመኗ ደርሼ፣ ወጥቼ ወርጄ በድንግልና የምትወልደውን ድንግል ባገለገልኳት" ብለሽ በትሕትና የተናገርሽ ደብር ነባቢት ሆይ! ሰውን የሚወድ፣ ሰውም የሚወደው ጌታ ባሕርዩ ሳይለወጥ ካንቺ ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ሰው ኾነ። እንደኛ የሚናገር ሥጋን ነሥቶም ሰው ኾነ። ጥበብን በሚገልጽ፣ ሥጋዌን በሚያስፈጽም በግብረ መንፈስ ቅዱስ አምላክ በማኅፀንዋ አደረና ፍጹም ሰው ኾነ። በቸርነቱና በይቅርታው ብዛት አዳምን ያድነው ዘንድ፣ ኃጢአቱንም ያስተሠርይለት ዘንድ፣ በሰማያዊ ቦታ በሰማያዊ መዓርግ ያኖረው ዘንድ /ኤፌ.፪፡፮/፣ ወደ ቀደመው ቦታው ወደ ቀደመው ክብሩ ይመልሰው ዘንድ ፍጹም ሰው ኾነ። በቸርነቱ በይቅርታው ብዛት አዳምን ወደ ቀደመው ቦታ ከመለሰው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፱. የድንግል ክብሯ ሊናገሩት አይቻልም። ከእናንተ መካከል፡- "ይኸው እየተናርን አይደለምን?" የሚል ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፡- "ለርሷ እንደሚገባ አድርጎ መናገር የሚቻለው የለም" ሲል

ነው። “ለምን?” ጌታ መርጧታልና። አሁንም ከእናንተ መካከል፦ “ታድያ እርሱ ከመረጣትማ ምን ይደንቃል?” የሚል ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፦ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ላይ፣ “በአማን ነጸረ እግዚአብሔር አብ እምሰማይ ምሥራቀ ወምዕራበ ሰሜነ ወደቡበ ወውስተ ኩሉ አጽናፍ አስተንፈሰ ወአጼነወ ወኢረከበ ከማኪ ወሠምረ መዐዛ ዚአኪ ወአፍቀረ ሥነኪ ወፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘያፈቅር - እግዚአብሔር አብ በሰማይ ኾኖ ምሥራቅንና ምዕራብን ሰሜንንና ደቡብን ዳርቻዎችን ኹሉ በእውነት ተመለከተ፤ ተነፈሰ፤ አሻተተም፤ እንዳንቺ ያለ አላገኘም። የአንቺ መዐዛ ወደደ፤ የሚወደውን ልጁንም ወደ አንቺ ላከ” ብሎ እንደተናገረው እንድትመረጥ ኾና ተገኝታለችና ነው /ቅዳ.ማር.ቁ.፶፬/።

ሐዋርያው “ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል” እንዲል /፩ኛ ጢሞ.፮፥፲፮/ በመመርመር ገንዘብ በማድረግ የሚቀርበው በሌለው ብርሃን ባሕርዩ አድሮ የሚኖረ እርሱ /ሃይ.አበ.፴፫፥፫/ ሰው ኾኖ በማኅፀንዋ አደረ /ዮሐ.፩፥፲፬/። ዘጠኝ ወር ከአምስተ ቀን በማኅጸንዋ ኖረ። ሰውም ከመኾኑ አስቀድሞ ሰውም ከኾነ በኋላ የማይመረመር እርሱን ማኅተመ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ወለደችው። ሰውም ከመኾኑ አስቀድሞ ሰውም ከኾነ በኋላ ከማይመረመረው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፲. ነቢዩ ዳንኤል ያየውና እጅ ሳይፈነቅለው ከረጅም ተራራ የወረደው ደንጊያ /ዳን.፪፥፭-፴፭/ ከአብ ዘንድ የወጣው አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ያ ድንጋይ የሰው እጅ ሳይነካው ከረዥሙ ተራራ እንደተፈነቀለ ኹሉ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ዘር ምክንያት ሳይኾነው ከድንግል ተወለደ። ዳንኤል በአምሳለ እብን (ደንጊያ) ካየው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፲፭. ሐሩረ ፀሓይ ያልወደቀባት፣ ነፋስ ያልወዘወዛት፣ ለታብቁል (ታብቅል) ባለው ቃል ከልምላሜ፣ ከጽጌ፣ ከፍሬ የተገኘች ዐፅቀ ሠሉስ (የማግሰኞ ቅርንጫፍ) አንች ነሽ /ኩፋ.፪፥፲፪/። እንዲህ ማለቱ ነው፦ “በዕለተ ሠሉስ የተገኙ ቅጠሎች፣ ቅርንጫፎች ፀሐይ እንዳላጠወለጋቸው፣ ነፋስ እንዳልወዘወዛቸው ኹሉ አንቺም የኃጢአት ፀሐይ አልለወጠሽም። በሥጋሽ፣ በነፍስሽ፣ በኅሊናሽም ድንግል ነሽ እንጂ” /መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ፣ ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን፣ ክፍል ፩፣ ገጽ ፲/። አባ ጊዮርጊሥም፦ “በበደል ምሣር የማትቈረጪ፣ ከኀጢአት ዐውሎ ነፋስ የተነሣ የማትነዋወጪ፣ ዘወትር ፍጹም የምትለመልሚ፣ በዘመኑ ኹሉ የምታፈሪ፣ በወሮች ኹሉ የምትለቀሚ፣ ከዕፅዋት ኹሉ ይልቅ የምታምሪ እመቤቴ ማርያም ሆይ! የተባረክሽ ዕፅ ነሽ” ይላታል /እንዚራ ስብሐት፣ ገጽ ፲፬/። አምላክን የወለድሽ ንጽሕት፣ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ኅትምት

የምትኾኝ ሆይ! ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ስለ ማዳን ሰው ኹኗልና (አካላዊ ቃልን ወልደሽልናልና) የሃይማኖትም (የክርስቶስም) ሙዳይ (መገኛ) ነሽ። (በልጅሽ ላመኑ) የአባቶቻችን የቀናች ሃይማኖታቸው ነሽ። እኛን ስለማዳን ሰው ከኾነ ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፲፪. የከበርሽ አምላክን የወለድሽ ሆይ! የማይመረመር ቃልን የወሰንሺው የብርሃን እናቱ አንች ነሽ። እርሱንም ከወለድሽው በኋላ ማኅተመ ድንግልናሽ ሳይለወጥ ኖረሻልና በአፍኣ በውስጥ በሥጋ በነፍስ ያከብሩሻል፤ ያገኑሻል። እንዲህ ካለ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፲፫. ወዮ! ስለ አንቺ ድንቅ ኾኖ የሚነገረውን ነገር መናገር የሚቻለው ምን አንደበት ነው? ቅድመ ዓለም ያለ እናት ተወልዶ፣ ድኅረ ዓለም ያለ አባት እንደምን እንደወለደሽው መናገር የሚቻለው ምን አንደበት ነው? የአካላዊ ቃል እናቱ ንጽሕት ደንግል ሆይ! ኪሩቤል ለሚሸከሙት ለንጉሥ ማደሪያ ኾንሽ። ንዕድ ክብርት ሆይ! እኛም ክብርሽን ገናንነትሽን ዕፁብ ዕፁብ እያልን እናመሰግንሻለን /ሉቃ.፩፡፵፰/። የአካላዊ ቃል እናቱ መልካሚ ርግብ (ርግበ ኖኅ) ማርያም ሆይ! ስምሽን በትውልደ ሴም፣ በትውልደ ካም፣ በትውልደ ያፌት እንጠራለን። ሊቁ እመ አምላክን "መልካሚ ርግብ" አላት። ይኸውም የኖኅ ርግብ "የጥፋት ውሃ ጐደለ፤ የጥፋት ውሃ ተገታ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰላም ነው" ስትል የምሥራቹን የዘይት ቅጠል ይዛ እንደታየች ኹሉ /ዘፍ.፰፡፲፩/ እመቤታችንም "የኅጢአት ውሃ ጐደለ፤ የመርገም ውሃ ተገታ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ዘመነ ሰላም ነው" ስትል ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔን ኣሳልፎ ዓመተ ምሕረትን የተካ፣ ለዓለሙ ኹሉ ታላቅ የምሥራች የኾነ፣ የዓለም መድኃኒት ክርስቶስን ወልዳልናለችና። እንዲህ ካለ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፲፬. እናትነትን ከአገልጋይነት ጋር /ሉቃ.፩፡፴፰/ ያለሽ እመቤታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ። በክንድሽ የያዝሺውን (የታቀፍሽውን) መላእክት ያመሰግኑታልና። እሳታውያን የኾኑ ሱራፌልም ሳያቋርጡ ከንፋቸወን ዘርግተው፡- "የክብር ባለቤት ይህ ነው" ይላሉ። "በቸርነቱ በይቅርታው ብዛት የሰውን ኹሉ ኃጢአት ለማስተሥረይ ሰው የኾነ የክብር ባለቤት ይህ ነው" እያሉ በፍርሐት በረዐድ ኾነው ያመሰግኑታል። የሰውን ኃጢአት በቸርነቱ ብዛት ከሚያሰተሠርይ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

ይህን ሲጨርስ በያዘችው መስቀለ ብርሃን ባርካው ታርጋለች። እርሱም ተባርኮ እጅ ነሥቶ ይቀራል።

አነሣሥቶ ላስጀመረን ፤ አስጀምሮም ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

የረቡዕ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ

ገ/እግዚአብሔር ኪደ

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ ነሐሴ ፭ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.)፡- ለምስጋና ሦስተኛ፣ ለፍጥረት አራተኛ ቀን በሚኾን በዚህ ዕለት ከወትሮ ይልቅ መላእክትን አስከትላ እመቤታችን ትመጣለችና፤ የብርሃን ድባብ ይዘረጋልና፤ የብርሃን ምንጣፍ ይነጸፋልና። ከዚያ ላይ ኾናም፡- “ሰላም ለከ ኦ ፍቁርየ ኤፍሬም” ትለዋለች። እሱም ታጥቆ እጅ ነሥቶ ይቆማል። ከባረከችው በኋላም ምስጋናዋን “ኵሉ ሠራዊተ ሰማያት ይብሉ ብፅዕት አንቲ...” ብሎ ይጀምራል።

፮. ኵሉ ሠራዊተ ሰማያት ይብሉ ብፅዕት አንቲ ሰማይ ዳግሚት ዲበ ምድር - ከምድር በላይ ያለሽ ኹለተኛ ሰማይ ሆይ! በሦስቱ ሰማያት (በኢዮር፣ በራማ፣ በኤረር) ያሉ መላእክት ንዕድ ነሽ፤ ክብርት ነሽ ይላሉ። ማርያም የምሥራቅ ደጅ ናት፤ ከእርሷ የጽድቅ ፀሐይ ክርስቶስ ተኝቷልና። ማርያም ሙሽራዋ ንጹሕ የሚኾን ንጽሕት የሠርግ ቤት ናት። በሠርግ ቤት የመርዓዊና የመርዓት (የሙሽራና የሙሽሪት) ተዋሕዶ ይደረግበታል። በእመቤታችንም እንደ መርዓዊና እንደ መርዓት ተዋሕዶ፤ ትስብእትና መለኮት አንድ ኾነዋልና። በሠርግ አዝማደ መርዓዊና አዝማደ መርዓት አንድ እንዲኾኑባት በእመቤታችንም ምክንያት ሰውና መላእክት፣ ሰውና እግዚአብሔር፣ ነፍስና ሥጋ፣ ሕዝብና አሕዛብ አንድ ኾነዋልና እመቤታችን ንጽሕት የሠርግ ቤት ናት /ኤፊ.፪፡፲፭/። አባ ሕርያቆስ “አስተንፈሰ ወአጼነወ ወኢረከበ ዘከማኪ፤ ወሠምረ መዓዛ ዚኣኪ ወአፍቀረ ሥነኪ ወፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘያፈቅር” እንዲል /ቅዳ.ማር.ቁ.፭፬/ አብ ከሰማይ ኾኖ አየ፤ ነገር ግን እንዳንች ያለ ባያገኝ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለውን ልጁን ሰዶ ካንቺ ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ሰው ኾነ። **ተቀዳሚ ተከታይ ከሌለው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና ሥርጉት (ክብርት) በቅድስና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።**

እዚህ ጋር አንዳንድ ወገኖች የሚያነሡትን ጥያቄ መልሰን እንለፍ። “ልመናስ ከዚያ በኋላ ስንኳን በሷ (ከበቁ በኋላ) በሌሎችም የለባቸውም። በቀደመ ልመናዋ የምታስምር ስለ ኾነ እንዲህ አለ እንጂ” ስለተባለ

ምሥጢሩን ሳይረዱ "ቅዱሳን በአጸደ ነፍስ አያማልዱም" ለማለት የሚጠቅሱት ወገኖች አሉ። የዚህ ኃይለ ቃል ትርጓሜ ግን ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የዕብራውያንን መልእክት በተረጐመበት በ፲፫ኛው ድርሳኑ ላይ፡- "ጻድቃን ይረክቡ ኩሎ በአሐቲ ተምኔቶሙ በአሐቲ ስእለት - ጻድቃን አንድ ጊዜ በለመኑት ልመና የሚሹትን ኹሉ ያገኛሉ" እንዳለው /ቁ.፱፯፱/ ቅዱሳኑ በአጸደ ሥጋ ሳሉ እግዚአብሔር አንድ ጊዜ "በስምሽ/ህ ለታረዙ ያለበሰ፣ ሕሙማንን የጐበኘ፣ ዝክርሽ/ህን የዘከረ..." እያለ በገባላቸው ቃል ኪዳን መሠረት በስማቸው የዘከረ፣ በስማቸው ሕሙማንን የጐበኘ፣ የመጸወተ እንደሚምርላቸው የሚያስረዳ ነው። ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር፣ ዓለምን ዳግም በንፍር ውሃ የማያጠፋትና በየዕለቱ ቀስተ ደመናን የምንመለከተው ፡- "ቃል ኪዳኔንም ለእናንተ አቆማለሁ፤ ሥጋ ያለውም ኹሉ ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም፤ ምድርንም ለማጥፋት ዳግመኛ የጥፋት ውኃ አይኾንም" ብሎ /ዘፍ.፱፥፲፩/ ለኖኅ አንድ ጊዜ በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት እንጂ ኖኅ በየዕለቱ እንዲህ ስለሚለምን አይደለም። "አይለምንም" ሲባል ግን ክብሩን፣ ልዕልናውን፣ መንፈሳዊ ብቃቱን የሚያስረዳ እንጂ ማማለድ አይችልም ለማለት አይደለም። እንደውም ይህ ኃይለ ቃል ከማማለድ በላይ የኾነ ክብር እንደተሰጣቸው የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም አንድ ጊዜ ለምኖ በየጊዜው የሚሹትን ማግኘት፤ ዕለት ዕለት እየለመኑ የሚሹትን ከማግኘት በላይ ልዕልናን፣ ክብርን፣ መንፈሳዊ ብቃትን ያሳያልና። አሁን ቅዱሳንን አማልዱን ስንላቸው አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው ደጋግሞ እንደገለጸው ቃል ኪዳናችሁን አሳስቡልን ስንል ነው /ቅዳ.ማር. ቁ.፱፷፱-፱፸፮ ይመልከቱ/።

፪. ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ነገር - ወደ ቀደመው ነገር እንመለስ። አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ! አንቺን ብቻሽን ትውልደ ሴም፣ ትውልደ ካም፣ ትውልደ ያፌት (ትውልድ ኹሉ) ያመሰግኑሻል /ሉቃ.፩፥፵፰/። ፱ ወር ከ፭ ቀን ማኅፀንሽን ዓለም አድርጐ የኖረብሽ ሀገረ እግዚአብሔር፣ መንግሥተ ሰማያት ሆይ! ነቢያት ላንቺ "ኢይትዐፀዉ አናቅጽኪ (በሮችሽ ኹል ጊዜ ይከፈታሉ - ንስሐ የሚገቡ ኃጥአንን ለመቀበል)፤ ወኢይጸልም ወርኀኪ (ጨረቃሽ አይቋረጥም)፤ ወኢየዐርብ ፀሐይኪ (ፀሐይሽ ከዚያ በኋላ አትጠልቅም - ፈጣሪሽ አያልፍም)፤ እስመ እግዚአብሔር ብርሃንኪ ለዓለም (ለዘለዓለም ብርሃንሽ እግዚአብሔር ነውና)" /ኢሳ.፷፡ ፲፰፣፳/፤ "ነኪር ነገሩ በእንቲአኪ ሀገረ እግዚአብሔር - የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ! ስላንቺ የተነገረው ነገር ድንቅ (ልዩ) ነው" /መዝ.፹፮፡፫/ እያሉ ድንቅ ድንቅ ነገርን ተናገሩልሽ። በርግጥም ሰማይና ምድር የማይችሉትን አምላክ የአንቺን ማኅፀን ከተማ አድርጎ ፱ ወር ከ፭ ቀን መኖሩ፤ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ አካላዊ ቃልን መፀነስሽ፤ በኅቱም ድንግልና መወለዱ፤ የድንግልና ጡቶችሽን ማጥባትሽ ድንቅ ነው።

ደስ ብሏቸው የሚኖሩ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ የመላእክት ማደሪያ ኹነሻልና የምድር ነገሥታት ይህን ዜናሽን ሰምተው፣ ጣዕመ መንግሥት ሰማያትን ምረረ ገሃነምን ዐውቀው መንነው ይሄዳሉ። እነርሱ ብቻ አይደሉም፤ ሠራዊቶቻቸውም ጣዕመ መንግሥት ሰማያትን ምረረ ገሃነምን ዐውቀው መንነው ይሄዳሉ። አንድም ብርሃን ልጅሽን አምነው ጸንተው ይኖራሉ። አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ! አንቺን ብቻሽን ትውልደ ሴም፣ ትውልደ ካም፣ ትውልደ ያፌት ያመሰግኑሻል /ሉቃ.፩፡፵፰/፤ ካንቺ ለተወለደውም ይሰግዱለታል፤ "ዐቢይ እግዚአብሔር - እግዚአብሔር ታላቅ ነው" እያሉም ያከብሩታል፤ ያገኑታልም። "ዐቢይ እግዚአብሔር" እያሉ ከሚያከብሩት ከሚያገኑት ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና ሥርጉት በቅድስና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

ፎ. "እንተ በአማን ንጹሕ ዝናም" የተባለ፣ የነፍሳትን ጥም ያበረደ የሕይወት ዝናም፣ የሕይወት ጠል፣ የሕይወት ውሃ ክርስቶስን ቋጥረሽ (በድንግልና ፀንሰሽ፣ በድንግልና ወልደሽ) የታየሽልን እውነተኛ ደመና አንቺ ነሽ። ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊሥ ዘጋሥጫም፡- "ንዑ እንከ ከመ ናልዕላ ለዛቲ ደመና ብርሃን እንተ ጾረቶ ለማየ ዝናም ንጹሕ- ንጹሑን የዝናም ውሃ የተሸከመችውን የብርሃን ደመና ኑ ከፍ ከፍ እናድርጋት" ብሎ ጋብዞናል /አርጋኖን ዘሠሉስ ፯፡፪/። ስትወልጂው ማኅተመ ድንግልናሽ አለመለወጡ፤ አካላዊ ቃል ሰው ሲኾን አምላክነቱ ላለመለወጡ፣ ድንግል ወእም (ድንግልም እናትም) ስትባዪ መኖርሽም ልጅሽ አምላክ ወሰብእ (ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው) ሲባል ለመኖሩ ምሳሌ ነውና አብ የልጁ ምልክት አደረገሽ። መንፈስ ቅዱስ ቢያድርብሽ፣ ኀይለ ልዑል ወልድም ሥጋሽን ቢለብስ፤ አንድም መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ ግብራት (ማለትም ከሩካቤ፣ ከዘር፣ ድንግልናን ከመለወጥ) ቢከለክልሽ፣ ኀይለ ልዑል ወልድም ከሦስቱ ግብራት ቢከልልሽ ለዘላለሙ የሚኖር አካላዊ ቃልን ወለድሽልን /ሃይ.አበ.፪፲፡፳፱/። እርሱም ሰው ኾኖ ከኃጢአት አንድም ከኃጢአታችን ፍዳ አዳነን።

ደስ ያለህ ባለ ምሥራች ገብርኤል ሆይ! ወደኛ የመጣ የጌታን ልደት ነግረኸናልና ላንተ የተሰጠ ክብር ፍጹም ነው። አንድም "ወነዋ ተወልደ ፍሰሐ ዘይከውን ለክሙ ወለኩሉ ዓለም - እነሆ ለሕዝቡ ኹሉ የሚኾን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁ" ብለህ /ሉቃ.፪፡፲/ የጌታን ልደት ለኖሎት (ለእረኞች) ነገርኸቸዋልና ለአንተ የተሰጠ ክብር ፍጹም ነው። "እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ካንቺ ጋራ አንድ ይሆናልና ደስ ይበልሽ" ብለህ /ሉቃ.፩፡፴/ ለእመቤታችን ነግረኻታልና ለአንተ የተሰጠ ክብር ፍጹም ነው። እንዲህ ካለ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና ሥርጉት በቅድስና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳነሣን ለምኚልን።

፱. መንፈስ ቅዱስ ቢያድርብሽ፣ ኃይለ ልዑል ወልድም ሥጋሽን ቢለብስ ጸጋን አገኘሽ። መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ ግብራት ቢከለክልሽ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ተብለው ከሚመሰገኑት ከሦስቱ አካላት አንዱን ቅዱስ ወለድሽልን። ሰውን ኹሉ የሚያድን እርሱም ሰው ኾኖ አዳነን። ሰው ኾኖ ካዳነን ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና ሥርጉት በቅድስና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

፲. ቀድሞ ከነበሩት ጋር አንድ ኾኖ አንደበታችን የድንግልን ሥራ ያመሰግናል። ዛሬ ካሉት ጋር ኾኖም እመቤታችንን ያመሰግናል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዳዊት አገር በዳዊት ባሕርይ ካርኋ ተወልዷልና። አሕዛብ ሆይ! ኑ እመቤታችንን እናመስግናት /ሃይ.አበ.፷፯፡፸/። እናትን ኹናለችና፤ ድንግልናም ደርባለችና ኑ እመቤታችንን እናመስግናት። አካላዊ ቃል ካንቺ ሰው የኾነ አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ ድንግል ሆይ! ደስ ይበልሽ። አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ ንጹሕ ሽቱ ዕቃ ሆይ! ደስ ይበልሽ። የሽቱን ዕቃ ጢስ እንዳይተንበት ትቢያ እንደይበንበት ቤት ሰፍተው፣ ሰቅለው፣ ተንከባክበው ያኖሩታል። እርሷንም "መንፈስ ቅዱስ ዐቀባ እምከርሠ እማ ከመ ኢትጌኒ - እንዳትበድል ድንግልን ከእናቷ ሆድ ጀምሮ የጠበቃት መንፈስ ቅዱስ እንዳትረክሰም ያነጻት ለወልድ ዋሕድም ማደርያ ያደረጋት እርሱ ነው" ይላታልና /አርጋኖን ዘእሑድ፣ ቁ.፲፰/። ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብም በነገረ ማርያም መጽሐፉ፡- "ንጽሕት ይእቲ እምኵሉ ትሕዝብት ወእምኵሉ ርስሐተ ኀጢአት - እርሷ (እመቤታችን) ከርስሐተ ኀጢአትና ከመጠራጠርም ኹሉ ንጽሕት ናት" ብሏል /ነገረ ማርያም በሐዲስ ኪዳን፣ ገጽ ፶፯-፶፯/።



ስለ ቀደመ ሰው (ስለ አዳም) ዳግመኛ አዳም የተባለ የክርስቶስ እናቱ ነባቢት ገነት ሆይ! ደስ ይበልሽ። ከአባቱ ዕሪና (አንድነት) ያልተለየ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው እርሱን የወሰንሺው በፍጹም ጌጥ ያጌጠች ንጹሕ የሰርግ ቤት ሆይ! ደስ ይበልሽ። የሰርግን ቤት አስቀድመው በሐር ያንቆጠቁጡልኟ ያነጽፉታልኟ ይጎዘጉዙታልኟ ሽቱ ያረበርቡበታልኟ ሐረግ ወርድ ይሥሉበታል። እንደዚህም ኹሉ አስቀድመን እንደተናገርን መንፈስ ቅዱስ

ድንግልን ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ ጠብቋታልና እንዳትረክሰም አንጽቷታልና እንዲህ አለ። አንድም በየጊዜው የጸጋ ክብር ይጨመርላታልና።

ባሕርየ መለኮቱ ያልለወጠሽ ዕፀ ጳጦስ ሆይ! ደስ ይበልሽ። (ዕፀ ጳጦስ ማለት በሀገራችን ደደሆ፣ እንጆሪ የምንለው ነው) /ዘጸ.፫፥፭-፫/። ቅዱስ ኤፍሬም የዚህን ግሩም ምሥጢር "ዲያቲሳሮን" በተባለ መጽሐፉ ሲተነትነው ፦- "ፈጣሪ ዓለማት ቅዱስ እግዚአብሔር የወደቀውን ፍጥረቱ ወርዶ ያነሣው ዘንድ፣ ቆሽሾ የነበረው ሕንፃዉንም (ሰውንም) ይወለውለው ዘንድ ተገቢ ነበር። በመኾኑም ፈጣሪ ራሱ በሰው ልጆች ላይ ፈርዶት የነበረውን ፍርድ የባሕርይ ልጁ እንዲሸከመው ካደረገ (በእርግጥም አድርጐታልና) የሰው ልጅ ወደ ጥንተ ተፈጥሮው ይመለሳል ማለት ነው (በርግጥም ተመልሷል)። ይህ አካላዊ ቃል፣ በሰው መተላለፍ ምክንያት በቅለው የነበሩት እሾክንና አሜኬላን ያቃጥል ዘንድ የመጣ ነባቢ ፍሕም ነው /ዘፍ.፫፥፲፰፣ ኢሳ.፱፥፲፰/። መጥቶም በማኅፀነ ድንግል አደረ፤ አነጻው፤ የጭንቅና የርግማን ቦታ የነበረው ማኅፀን ቀደሰው /ዘፍ.፫፥፲፯/። ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ ያየው ነበልባል ሐመልማሉን አላጠፋውም፤ ይልቁንም እንዲለመልም አደረገው እንጂ /ዘጸ.፫፥፪-፫/። የነጠረ ወርቅ የሚመስል አካልም ወደ ነበልባሉ ገባ፤ ኾኖም አሁንም እሳቱ አልፈጀውም። ይኸውም በዘመኑ ፍጻሜ ሊመጣ ላለው ነባቢ እሳትና የድንግልን ማኅፀን አለምልሞ ቁጥቋጦውን እንደከደነውም እንደሚከድናት የሚያስረዳ ነው" ብሏል። ዳግመኛም አባ ጊዮርጊሥ ዘጋሥጫ የእሳተ መለኮት መምጣት ምክንያቱ ሲገልጽ፦- "... (ጌታችንም) የዓለምን ኃጢአት በትከሻው ተሸክሞ ወደ ዕፀ መስቀል ወጣ።... ያን ጊዜ እግዚአብሔር እሾኽና አሜኬላ ይብቀልብህ ብሎ በረገመው ጊዜ በአዳም ሥጋ የበቀለ የኃጢአት እሾኽ ተቃጠለ" ብሏል /መጽሐፈ ምሥጢር ፲፱፥፳፩/።

በኪሩቤል አድሮ የሚኖረው ሰማያዊ መለኮትን በሥጋ የተሸከምሽው ማኅደርም የተባልሽ እመቤትነትን ከገረድነት፣ እናትነትን ከድንግልና ጋር አስተባብረሽ የያዝሽ ሰማይ ሆይ! ደስ ይበልሽ። ስለዚህ ነገር፦- "አምላክ ለኾነ ለሥጋ ከሥላሴ ጋራ በአንድነት ምሥጋና ይገባዋል፤ በምድርም ዕርቅ ተወጠነ" እያልን ንጹሐን ከኾኑ መላእክት ጋር በፍጹም ደስታ ደስ ተሰኝተን እናመሰግን። ክብር የክብር ክብር ያለው እርሱ አንቺን ለእናትነት መርጧልና ንጹሐን ከኾኑ መላእክት ጋር በፍጹም ደስታ ደስ ተሰኝተን እናመሰግን /ሉቃ.፪፥፲/። አንቺን ለእናትነት ከመረጠ ልጅሽ ጽንዕት ሥርጉት በቅድስና በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳነሳን ለምኚልን።

፮. ከቅዱሳን ክብር የእመቤታችን ክብር ይበልጣል። አካላዊ ቃልን ለመቀበል በቅታ ተገኝታለችና።መላእክት

የሚፈሩትን፣ ትጉሃን በሰማያት የሚያመሰግኑትን ድንግል ማርያም በማኅፀንዋ ቻለችው። እንዲህም ከኾነ ከመላእክት ትበልጣለች፤ ከሱራፌልም ትበልጣለች፤ ከሦስቱ አካል ላንዱ ማደሪያ ኾኖለችና። ኢትዮጲያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ይህን በጥኅተ ብርሃን መጽሐፉ ላይ ሲገልጽ "አንቲ ተዓብዩ እምኪሩቤል ወትፈደፍዲ እምሱራፌል፣ እምሱራፌል ወኪሩቤል በሠረገላ እሳት ይጸውርዎ ወበምጽንዐ እሳት ይጼንዑ መንበሮ፤ ወአንቲሰ ጾርኪዮ በከርሥኪ ወሐዘልኪዮ በዘባንኪ ወሐቀፍኪዮ በአብራክኪ ህየንተ ሠረገላ እሳተ አብራክኪ ኮነ ወህየንተ ምጽንዐቲሁ ዘእሳተ እደውኪ ኮና - ከኪሩቤል ይልቅ አንቺ ትበልጫለሽ፤ ከሱራፌልም ይልቅ አንቺ ትልቂያለሽ፤ ኪሩቤልና ሱራፌል በእሳት ሠረገላ ተሸክመውታልና፤ አንቺ ግን በማኅፀንሽ ወሰንሺውን፤ በዠርባሽም አዘልሺውን፤ በጉልበቶችሽም ዐቀፍሽውን፤ ጉልበቶችሽም እንደ እሳት ሠረገላ ኾኑ፤ እጆችሽም እንደ እሳት አዕማድ ኾኑ" በማለት የተሰጣት ክብር ከኪሩቤል ከሱራፌል የበለጠ መኾኑን አስተምሯል።

የነቢያት ሀገራቸው ኢየሩሳሌም ይህች ናት። መንግሥተ ሰማያትን የሚያወርሰን ከእርሷ በነሣው ሥጋ ምክንያት ነውና ደስ ብሏቸው የሚኖሩ የጻድቃን፣ የሰማዕታት፣ የመላእክት ማደሪያቸው ይህቺ ናት። በድንቁርና በቀቢፀ ተስፋ ለነበሩ ሰዎች ዕውቀት ተሰጣቸው፤ ክርስቶስ ተወለደላቸው /ኢሳ.፱፡፪/። ወንጌል ተጻፈላቸው /ሉቃ.፩፡፩-፬/። በቅዱሳን አድሮ የሚኖር እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ሰው ኾኗልና በሞተ ሥጋ፣ በሞተ ነፍስ ለነበሩ ሰዎች ልጅነት ተሰጣቸው /ዮሐ.፩፡፲፪/። በኃጢአት በክሕደት ለነበሩ ሰዎች ሃይማኖት (አሚን) ተሰጣቸው /ማቴ.፬፡፲፬/። ተወዳጆች ሆይ! ይህን ድንቅ ምሥጢር ኑ እዩ። ስለ ተገለጸን ምሥጢር ምስጋና አቅርቡ። ከዚህ ቀደም ሰው ኾኖ የማያውቀው እንግዲህም ወዲህ ሰው ማይኾነው ሰው ኾኗልና ይህን ድንቅ ምሥጢር ኑ እዩ። ቃል ከሥጋ ጋር ቢዋሐድ ጥንት የሌለው መለኮት ፭ ሺሕ ከሯ፪ ዘመን ሲፈጸም ዘመን ተቀድሞት ወደ ኋላ ተገኘ። ቅድምና የሌለውም ሥጋ ቀዳማዊ አምላክ ተባለ። አንድም ጥንት (ቅድምና) የሌለው ሥጋ ቀዳማዊ አምላክ ተባለ። ዘመን የማይቆጠርለትም መለኮት ፲፪ ዓመት ኾነው /ሉቃ.፪፡፵፪/፤ ፴ ዓመት ሞላው ተብሎ ዘመን ተቆጠረለት /ሉቃ.፫፡፳፫/። አንድም አካላዊ ቃል በጎላ በተረዳ ሰው ኾኗልና በኩር ያልነበረ መለኮት በኩር ተባለ /ማቴ.፩፡፳፭/። ክብር የሌለውም ሥጋ ክቡር አምላክ ተባለ። በገዥነት የማይታወቅ ሥጋ በገዥነት ታወቀ፤ በተገዢ ሥጋ ታይቶ የማይታወቅ መለኮትም በተገዢ ሥጋ ታየ። ቅድመ ዓለም የነበረው፣ በማዕከለ ዓለም ያለው፣ መቼም መች የሚኖረው ኢየሱስ ክርስቶስ እንሰግድለትና እናመሰግነው ዘንድ ከአብ ከባሕርይ አባቱ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ ጋራ አንድ ባሕርይ ነው። ከአብ ከባሕርይ አባቱ ከመንፈስ ቅዱስ ከባሕርይ ሕይወቱ ጋራ አንድ ባሕርይ ከሚኾን ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና ሥርጉት በቅድስና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንደይነሣን ለምኚልን።

፯. ነቢዩ ሕዝቅኤል የእርሷን ነገር “በድንቅ ቁልፍ የተቈለፈች ደጅ በምሥራቅ አየሁ” ብሎ ተናገረ /ሕዝ.፵፬፥፩-፪/። ከእግዚኣ ኃያላን በቀር ሳይከፍታት ገብቶ ሳይከፍታት የወጣ የለም። እግዚአ ኃያላን እሱ ሳይከፍታት ገብቶ ሳይከፍታት ወጣ እንጂ። እግዚአ ኃያላን ከሚባለው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና ሥርጉት በቅድስና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን አንዳነሣን ለምኚልን።

፰. ኖኅትም (ድጅም) የተባለች መድኃኒታችንን ጌታን የወለደችልን ድንግል ናት። እሱን ከወለደችው በኋላ እንደ ቀድሞ ማኅተመ ደንግልናዋ ሳይለወጥ ኑራለቸና። ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግም፥- “... አንተ መናገር የተሰጣቸውን ሠረገሎች ድምፅ የሰማህ ባለ ሞገስ ሆይ (ሕዝ.፫፥፲፫)! እንደዚሁም የክንፎቻቸውን ድምፅና የዚያን ሠረገላ ታላቅ እንቅስቃሴ የሰማህ ሆይ (ሕዝ.፲፥፭)! አንተ የኪሩቤልን መልክ መለወጥ ያየህ የበራልህ ነፍስ ሆይ! እንዲሁም እኒያ የእሳት ላንቃዎች በክፍታ ላይ የተቀመጠውን ሲያመሰግኑ የሰማህ ሕዝቅኤል ሆይ (ሕዝ.፩፥፬-፳፭) ና! አንተ የቡዝ ልጅ ሆይ (ሕዝ.፩፥፫፪) ና! የተጠቀለለውን የትንቢትህን ቃል ብራና አምጣልን። አንተ ቁምና እውነትን ተናገር፤ ሌሎቻችን ኹሉ ዝም እንበል። ካየኻቸው ራዕዮች መካከል ድንግል ማርያም ታይታህ እንደኾነ፤ ፍጥረት ኹሉ ውበቷን ያይ ዘንድ መልኳን ግለጥልን። በትንቢትህ ውስጥ የጌታህን እናት የሚመለከት አንዳች ነገር ካለ ይህ ለሚሰሙት እጅግ ውድ ስለኾነ ተነሣና አብራራልን። ይህም ያም (መናፍቅ) ከመውለዷ በኋላ ድንግል አልነበረችም በማለት ይናገራልና እውነት ድንግልናዋን አጥታ እንደኾነ እስኪ አንተ አስረዳን። ሕዝቅኤል ሆይ! ዛሬ የአንተ ተራ ነውና እስኪ ተናገር። ስለ እመቤታችን ማርያም ተናገርና ከንቱ ምርምሮችን ግታልን። እስከ አሁን በትንቢት ተነግሮ የነበረው ምን እንደነበር እንስማ። የማትመረመር ስለኾነችው ስለ ድንቅ እናታችን ይህ ነቢይ በትንቢቱ ውስጥ እንዲህ ተናግሮ ነበር፥- ‘ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተ ውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፤ ተዘግቶም ነበር። እግዚአብሔርም። ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፥ ሰውም አይገባበትም፤ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል።’ አንተ የመንፈስ ነቢይ ሆይ! ይህ ቃል ምን ማለት እንደኾነ እስኪ ገልጠህ አብራራልን። በትንቢት የተነገረው የተዘጋው በር ድንግል ማርያም ናት። ምክንያቱም መሲሑ ጌታ በእርሱ በኩል ወደ ዓለም መጥቶ ዝግ አድርጎ ትቶታልና። ጌታ በዚህ በር ሲገባ እንዳልከፈተው ዕብራዊ የኾነ ሕዝቅኤል ከእኛ ጋር አብሮ ይህንኑ ይመሰክራል። እግዚአብሔር እንደወደደው በመውለድ በር ወደ ዓለም ገባ። ያንንም በር በድንግልና ዘጋው። ነቢዩ በሩ ተዘግቶ ያየው ያ ቤተ መቅደስ ስለ ድንግልናና ስለማይለወጥ ድንግልናዋ የሚያሳየን ነው። ቅዱሱ መሲሑ (ክርስቶስ) ሲኾን ቤተ መቅደሱም ማርያም ናት።

የተዘጋውም በር በእርሷ የሚኖረውና ተፈትሖ የሌለበት የድንግልዋ ማኅተም ነው” ብሏል /Jacob of Serug, Homily on the Perpetual Virginity of Mary, pp VII-X/።

የማኅፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚያድል ነው። ለሰው ከማያዝን ከማይራራ፤ አንድም ለእርሱ ከሥላሴ ዘንድ ምሕረት ከሌለው፤ አንድም ታጢአቱን ሸልጎ ከማይሠራ ከዲያብሎስ እጅ ያዳነን ጌታችንን የወለድሽው ሆይ! በደንግሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ፍጽምት ነሽ። መርገም ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለብሽ /ኢሳ.፷፩፥፱/ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ እያማለድሽ የምታሰጭ ነሽ። ጌትነቱ እንደ ነገሥታት በጉልበት፣ እንደ ካህናት በሀብት፣ እንደ ጣዖታትም በሐሰት ባይደለ በክብር ባለቤት ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሸልና በዚህ ዓለም ከሚኖሩ ሰዎች ኹሉ ይልቅ ክብር ላንቺ ይገባል። አካላዊ ቃል መጥቶ ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ሰው ኾነ። ሰው ሰውኛውንም ኖረ። መሐሪ፣ ይቅር ባይ፣ ሰው የሚወደው ሰው ወዳጅ ነውና በልዩ አመጣጡ መጥቶ አዳነን። “አኮ በተንባል ወአኮ በመልአክ አላ ለሊሁ እግዚእ መጸእ ወያድኅነነ - በአማላጅ አይደለም፤ በመልአክም አይደለም። እርሱ ራሱ፣ በራሱ ደም፣ በራሱ ሊቀ ካህንነት መጥቶ ያድናቸዋል እንጂ ” /ኢሳ.፷፫፥፱/ እንዲል እንደ ቀደመው በረድኤት ሳይኾን በኩነት (ሰው ኹኖ) መጥቶ አዳነን። አንድም አምስት ሺሕ ካምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም አንድ ሰዓት ስንኳ ሳያሳልፍ በጽኑ ቀጠሮው መጥሮ አዳነን። በጽኑ ቀጠሮ መጥቶ ካዳነን ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና ሥርጉት በቅድስና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

የዓርብ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ

- ገ/እግዚአብሔር ኪደ

- **(መቅረዝ ዘተዋሕዶ ነሐሴ ፲ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም)፦** ይህ ዕለት ለምስጋና አምስተኛ ለፍጥረት ስድስተኛ ቀን ነው። በዚህም ቀን እመቤታችን ትመጣለች፤ የብርሃን ድባብ ይዘረጋል፤ የብርሃን ዙፋን ይነጸፋል። ከዚያ ላይ ኹናም ሊቁን ባርካው ምስጋናዉን ጀምሯል። ከወትሮ ይልቅም ደናግልን አስከትላ መጥታለች።

- ፩. ከሴቶች ተለይተሽ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ሌለብሽ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን እያማለድሽ የምታሰጭ ነሽ /ሉቃ.፩፡፳፰/። ቤዴ የተባለ ተርጓሜ መጻሕፍት ይህን አንቀጽ ሲተረጉመው፡- "የመጀመርያው የሰው ልጆች ስሕተት ከዲያብሎስ በእባብ አማካኝነት ወደ ሴት ተላከ። ሴቲቱም በትዕቢት መንፈስ ወደቀች። ዲያብሎስ በእባብ ገላ ተሰውሮ መጣና የመጀመርያዎቹ ወላጆቻችንን አታለላቸው። ኢመዋቲው ጸጋቸውን ገፈፈው። ስለኾነም ሞት በሴት ምክንያት ገብቷልና መድኃኒትም በሴት ምክንያት ይገባ ዘንድ ይገባው ነበር። ቀዳማይቱ ሔዋን ዲያብሎስ በእባብ ገላ ተሰውሮ አታለላት። ለሰውም ኹሉ የሞትን ጣዕም አቀመሰችው። ሌላይቱ ሔዋን ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ በተላከ መልአክ የዓለም መድኃኒት የኾነው ክርስቶስን አስገኘች" በማለት እመቤታችን ከሴቶች ኹሉ የመለየቷን ምሥጢር በጥልቀት አስተምሯል።
- የማኅፀንሽም ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍሰ የሌለበት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስ የሚያድል የባሕርይ አምላክ ነው። የሚላን ሊቀ ጳጳስ የነበረውና አምብሮስ የተባለው ሊቅ ይህን አንቀጽ ሲተረጉም፡- "እመቤታችን አመነች እንጂ አልተጠራጠረችም፤ በመኾኑም የእምነቷን ፍሬ አገኘች። "ወብጽዕት አንቲ እንተ ተአምኒ ከመ ይከውን ቃለ ዘነገሩኪ እም ኀበ እግዚአብሔር - ከእግዚአብሔር አግኝተው የነገሩሽን ነገር እንዲደረግ የምታምኚ አንቺ ንዕድ ክብርት ነሽ" እንዲል /ሉቃ.፩፡፵፭/። እናንተ ከእግዚአብሔር አግኝተው የነገርዋችሁን ነገር እንዲደረግ የምታምኑም ንዑዳን ክቡራን ናችሁ። የሚያምኑ ነፍሳት አካላዊ ቃልን ይፀንሱታል፤ በግብራቸውም ይወልዱታል (ይገልጡታል)። እንግዲያውስ እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ ታደርጉት ዘንድ እመቤታችንን ምሰልዋት። በፈጣሪያችሁ በመድኃኒታችሁ አምናችሁ ደስ ይላችሁ ዘንድ የእመቤታችንን ልቡና ገንዘብ አድርጉ /ሉቃ.፩፡፵፮-፵፯/። ምንም እንኳን ጌታችንን በሰውነቱ የምትወልደው (የወለደችው) እመቤታችን ብቻ ብትኾንም በእምነት በኩል ግን የኹሉም አማንያን ፍሬ ነውና" በማለት ይመክረናል።
- አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ! የጽድቅ ፀሐይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካንቺ ተወልዶም /ሚል.፬፡፪/ በክንፈ ረድኤቱ (በሥልጣኑ) አቀረበን። በሐዲስ ተፈጥሮ፣ በጥንተ ተፈጥሮ ፈጥሮናልና። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም እንዲህ ይላል፡- "በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከግብርናተ ዲያብሎስ ነጻ ወጣን። በግብረ መንፈስ ቅዱስ ውሉደ እግዚአብሔር ተባልን። ከምንም በላይ ግን ከኀጢአት ቀንበር ተላቅቀን በሐዲስ ተፈጥሮ ተፈጠርን። ሥርየተ ኀጢአትን ሰጠን። ከርኩሰት ኹሉ አነጻን። ከጸጋው የተነሣ ደቂቀ አዳም የነበርን መላእክት አደረገን። መላእክቱም ለእኛ በተደረገው ነገር ሐሴት

አደረጉ። ወዮ! ገና ሰዎች ሳለን መላእክት መኾናችን እንደምን ይረቃል እንደምን ይደንቃል? ይህ ኹሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው" /Fr. Tadros Malaty, On the Book of Isaiah 40:31/። በሐዲስ ተፈጥሮ፣ በጥንተ ተፈጥሮ ከፈጠረን ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

- ፪. አምላክን የወልድሽ እመቤታችን ሆይ! ፀሐይ ዘኢየዐርብ (የማይጠልቅ ፀሐይ) የተባለው የብርሃን ክርስቶስ እናቱ ነሽና በአፍኣ በውሰጥ በሥጋ በነፍስ አንቺን ብቻሽን እናከብርሻለን፤ እናገንሻለንም። ልዑላን ከሚባሉ መላእክት አንቺ ትበልጫለሽ፤ ትሑታን ከሚባሉ ከደቂቀ አዳምም አንቺ ትበልጫለሽ። ከኀሊናት ኹሉ በላይ ነሽ (ኀሊና የአንቺን ክብር ተናግሮ መጨረስ አይቻለውም)። ክብርሽን ገናንነትሽን መናገር የሚቻለው ማነው? አንቺንስ የሚመስል ማነው? ሊቁ አባ ሕርያቆስም፦ "ይህንም ባሰብኩ ጊዜ ኀሊናዬ የልጅሽን የባሕሩ ጥልቅነት ይዋኝ ዘንድ ይወዳል፤ የወዳጅሽ የመሠወሪያው ማዕበልም ያማታዋል" ይላል /ቅዳ.ማር.ቁ.፹፬/። መላእክት ያከብሩሻል፤ ያገኑሻልም። ሱራፌልም ያመሰግኑሻል። በኪሩቤል በሱራፌል አድሮ የሚኖረው እርሱ ሰው ኹኖ በማኅፀንሽ አድሯልና። ክብር የክብር ክብር ያለው እርሱ፤ ሰውን የሚወድ ሰውም የሚወደው እርሱ የእኛን ሞት ነሥቶ የእርሱን ሕይወት ለኛ ሰጥቶ ካባቱ ጋራ አስታረቀን። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በ "በእንተ ልደት" ድርሳኑ ላይ፦ "ስለዚህ ሥጋዬን ተዋሐደ! ወንጌልን ሲያስተምር እሰማው ዘንድ ሥጋዬን በተዋሐዶ ገንዘቡ አደረገው! ሥጋዬን ወስዶም መንፈሱን ሰጠኝ። ሰጠሁ፤ ተቀበልኩም። የእኔን ወስዶ የራሱን ስለ ሰጠኝም ሕይወትን ገንዘብ አደረግሁ። እኔን ለመቀደስ ሥጋዬን ተዋሐደ፤ የሚያድነኝ መንፈስ ቅዱስንም ሰጠኝ" ብሏል። ክብር የክብር ክብር ካለው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋዉን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፫. ድንግል ሆይ! የደናግል ኹሉ መመኪያቸው አንቺ ነሽ። ከእናንተ መካከል "መመኪያነቷ እንዴት ነው?" ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፦
- ሸ) ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ሲል ይመልስልናል፦ "ወበከመ አውዕአ ብእሲ ብእሲተ ዘእንበለ ብእሲት ከማሁ አውዕአት ብእሲት ብእሴ ዘእንበለ ብእሲ ወሀሎ ዕዳ ላዕለ ትዝምደ አንስትኒ፤ ወበእንተዝ ኮነት ፈዳዩተ ዕዳሃ ለሔዋን - ለወንዶች የሚከፈል ዕዳ በሴቶች ላይ ነበረ፤ ያለ እናት ሔዋን ተገኝታ ነበርና። ስለዚህም የሔዋንን ብድራት ለአዳም ትከፍለው ዘንድ ድንግል ያለ ዘርዐ ብእሲ (ያለ ወንድ ዘር) ክርስቶስን ወለደችው። አዳም ያለ እናት ሔዋንን ስላስገኘ

እንዳይመካ ድንግል ያለ አባት ክርስቶስን ወለደችው። ድንቅ በሚኾን አንድነት ይህ አንድ የፍጥረት እኩልነት ይታወቅ ዘንድ" /ሃይ.አበ.፷፯፡፸፱/፤

- ፪ኛ) ቀድሞ ወንዶች ሴቶችን በእናንተ ምክንያት ከገነት ወጣን እያሉ ርስት አያካፍሏቸውም ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ፡- "ብእሲ ወብእሲት አሐደ እሙንቱ በክርስቶስ - ወንድም ሴትም የለም፤ ኹላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና" ብሎ እስኪያስተምር ድረስ /ገላ.፫፡፳፰/ በሔዋን ምክንያት ከገነት ብትወጡ በእመቤታችን ምክንያት ገነት መንግሥተ ሰማያት ገብታችሁ የለምን? ብለው የሚመኩ ኹነዋልና፤
- ፫ኛ) ደግሞ ለደናግላን አስበ ድንግልናቸውን (የድንግልናቸውን ዋጋ) ስለምታሰጣቸው ሊቁ "ምክሆን ለደናግል" ብሏታል።
- ቅድመ ዓለም የነበረ እርሱ ሰው ኹኗልና (ካንቺ ተወልዷልና) የእኛን ሥጋ ነሥቶ የርሱን ሕይወት ሰጥቶ ከርሱ ጋራ አስተካከለን። በቸርነቱ ብዛት እንድንመስለው አደረገን /ፊል.፫፡፲-፲፩/። ከብዙ ሴቶች አንቺ ትበልጫለሽ። ክብር የክብር ክብር ካላቸው ከብዙ ሴቶች አንቺ ትበልጫለሽ /ሉቃ.፩፡ ፵፫/። ንጉሥ በከተማው እንዲኖር ዘጠኝ ወር ካምስት ቀን ማኅፀንሽን ዓለም አንድርጎ ኖሮብሽልና አምላክን የወለድሽ ድንግል ማርያም ሆይ! ልዑል እግዚአብሔር የከተመብሽ ረቂቅ ከተማ ነሽ። በኪሩቤል በሱራፌል አድሮ የሚኖረው እርሱን በማኽል እጅሽ ይዘሽዋልና ልዑል እግዚአብሔር የከተመብሽ ረቂቅ ከተማ ነሽ። በቸርነቱ ብዛት ፍጥረቱን ኹሉ በዝናም አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ የሚመግበው እርሱ ጡትሽን ይዞ ጠባ። አንድም ለሰውን (ለመንፈሳውያን) ኹሉ ሥጋውን ደሙን ሰጥቶ የሚመግበው እርሱ ጡትሽን ይዞ ጠባ። ይኸውም ፈጣሪያችን መድኃኒታችን ነው። እንሰግድለት እናመስግነውም ዘንድ በሐዲስ ተፈጥሮ በጥንተ ተፈጥሮ ፈጥሮናልና ለዘለዓለሙ ይጠብቀናል /ዮሐ.፮፡፶፯/። ሰጊድ (አምልኮ) ከሚገባው ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፬. ድንግል ማርያም ዕፍረተ ምዑዝ (መዓዛው የጣፈጠ) የተባለ ጌታችንን የወለደች ሙዳየ ዕፍረት (የሽቱ መኖርያ) /፷ኛ ሳሙ.፲፡፭ አንድምታው/፤ ዳግመኛም የማየ ሕይወት (የሕይወት ውኃ የክርስቶስ) ምንጭ ናት /መኃ. ፬፡፲፪ አንድምታው/። የማኅፀኗ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ኹሉ አድኗልና። ከእኛ መርገመ ሥጋን መርገመ ነፍስን አጠፋልን። ሐዋርያው ጳውሎስ፡- "በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ኹሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና" እንዲል

/ቈላ.፩፥፲፱-፳/ በመካከል ኾኖ በመስቀሉ አስታረቀን። ልዩ በኾነ ትንሣኤውም ሰውን ዳግመኛ ወደ ገነት መለሰው። ከእናንተ መካከል፦ “ልዩ በኾነ ትንሣኤ ሲል ምን ማለቱ ነው?” ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፦ ከእነ አልዓዛር ትንሣኤ የተለየ መኾኑን ለማሳየት ነው። ምክንያቱም፦

- ፩ኛ) እነ አልዓዛር አስነሺ ይሻሉ፤ እርሱ ግን “ላኖራት ሥልጣን አለኝ፤ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ” ብሎ እንደተናገረ /ዮሐ.፲፥፲፰/ የተነሣው በገዛ ሥልጣኑ ነውና። በተለያየ ሥፍራ “አብ አንሥኦ (አብ አስነሣው)፤ መንፈስ ቅዱስ አንሥኦ (መንፈስ ቅዱስ አስነሣው)” ቢልም አንድ ነው። ምክንያቱም ዕሪናቸውን መናገር ነውና።
- ፪ኛ) የእነ አልዓዛር ትንሣኤ በብሉይ ሥጋ ነው፤ የእርሱ ግን በሐዲስ ሥጋ ነው።
- ፫ኛ) የእነ አልዓዛር ትንሣኤ ሞትን ያስከትላል፤ የእርሱ ግን ሞትን አያስከትልም።
- ፬ኛ) የእነ አልዓዛር ትንሣኤ ትንሣኤ ዘጉባኤን ይጠብቃል፤ የእርሱ ግን አይጠብቅምና።
- **አዳምን ዳግመኛ ወደ ገነት ከመለሰ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።**
- ፭. አንዳንድ ተረፈ ንስጥሮሳውያን እንደሚሉት ንጽሕት ድንግል ማርያም ላቲ ስብሐትና “ወላዲተ ሰብእ” አይደለችም፤ የታመነች አምላክን የወለደች ናት እንጂ። የመናፍቃን መዶሻ የተባለው፣ በተለይም የቅድስት ድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት የካደውን ንስጥሮስን የረታው ቅዱስ ቄርሎስ እሳተ መለኮት አምላክን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀኗ የተሸከመች፣ በጀርባዋ ያዘለች፣ በዝናብ አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ የፈጠረውን ፍጥረት የሚመግበው አማኑኤልን የድንግልና ጡቶቿን ወተት የመገበችውን የወላዲተ አምላክን ክብር ያልተረዱትን ንስጥሮሳውያን መናፍቃንን ሲወቅስ “ወለዛቲ እንተ መጠነዝ ዐባይ ጾረት መለኮተ እፎ ይክልኣዋ እምክብራ ለወላዲተ አምላክ ወላዲተ አምላክኬ ቅድስት ድንግል - ይኸንን ያኽል ታላቅ ኾና መለኮትን የተሸከመችቱን የአምላክ እናት ክብርን እንደምን ይነፍጓታል፤ ይከለክሏታል። የአምላክ እናት ማለት ድንግል ማርያም ናታ” በማለት የተሰጣትን ክብር በማድነቅ አስተምሯል /ተረፈ ቄርሎስ/።
- እንዲህም ስለኾነ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የታመነች የምሕረት አማላጅ ናት። የዚህ ዓለም ሰዎች አማልዱኝ ቢባሉ ነገር አጽንተው ይመለሳሉ፤ እርሷ ግን “ማእምንት ሰአሊተ ምሕረት - የታመነች የምሕረት አማላጅ ናት” /ዮሐ.፪፥፭-፲፩/። ሰአሊተ ምሕረት ሆይ! ኃጢአታችንን

ያስተሠርይልን ዘንድ ከልጅሽ ዘንድ አማልጅን። ኃጢአታችንን ከሚያስተሠርይልን ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

- ፯. ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ አሰምታ ትናገር ነበር። አረጋዊው ዮሴፍ በግብረ መንፈስ ቅዱስ እንደ ፀነሰች ሳያውቅ "ኦ ወለተ እስራኤል መኑ ቀረፀ አክናፈ ድንግልናኪ" ቢላት "እኔስ ምልዕተ ክብር ሆይ! እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍሽ ነፍስ ነሥቶ አንድ አካል ይኾናል ብሎ መልአኩ አክብሮ ከነገረኝ ነገር በቀር ምን ምን የማውቀው እንደ ሌለኝ እግዚአብሔር ያውቃል" ብላ አሰምታ ተናገረች። ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም "ዲያተሳሮን" በተባለ የወንጌል ትርጓሜ መጽሐፉ የእመቤታችንና የዮሴፍ ግንኙነት እንዲህ በማለት በጥልቀት ተንትኖታል፡- "የመሲሑ ልደት እንዲህ ነበር። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች /ማቴ.፩፡፲፰/። ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ይህንን ያለ ምክንያት አይናገረውም። አሕዛብ አማልክቶቻቸው እጅግ አሳፋሪ በኾነ ግንኙነት እኛ ከምናውቀው ተፈጥሮ ውጪ ልጅ ይወልዳሉ ብለው ስለሚያስቡ እንጂ። በመኾኑም እነዚህ አሕዛብ እንደሚያስቡት እመቤታችን ፀንሳ ተገኘች ተብሎ እንዳይታሰብ ወንጌላዊው "ሳይገናኙ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች" አለ። የተወለደው በወንድ ዘር አይደለም። ማኅተመ ድንግናዋን ሳይለውጥ ገባ፤ አከበራትም፤ ነፍስና ሥጋም ከእርሷ ነሥቶ ተዋሐደ።
- አስቀድማ ለወንድ መታጨቷ፣ ባል (ጠባቂ) እንዳላት መደረጓ፣ ቀጥሎም መፅነሷ ልጇ ወዳጇ በዳዊት በትረ ሥልጣን ስለሚገባና የዳዊት ሥልጣንን የሚይዝ ደግሞም በእናቱ ሳይኾን በአባቱ ስም ስለሚጠራ ነው /ሉቃ.፩፡፴፪/። ከዚህም በተጨማሪ ክፉዎች የፀነሰችው በሴሰኝነት ነው ብለው እንዳያስቡ ነው። እጅግ ጻድቅ ለኾነው ለዮሴፍ የመታጨቷ ምክንያት ይህ ነበር። ዮሴፍ እመቤታችንን ፀንሳ ባያት ጊዜ እስክትወልድ ድረስ ተከባከባት። ከእርሷ ጋር በቤቱ ኖረ እንጂ አላባረራትም። ከማንምና ከምንም አስቀድሞ ከእርሷ የተፀነሰው በግብረ መንፈስ ቅዱስ እንጂ በዘርዐ ብእሲ እንዳልኾነ ምስክር ኾነ።
- እመቤታችንም ያለ ታራሽ ልጇን ወለደችው። ቀዳማይቱ ሔዋን አዳም ከማንም ጋር ሳይገናኝ እንደወለዳት አሁንም የዮሴፍና እመቤታችን በግብር ሳይተዋወቁ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ወለደች። ሔዋን ነፍሰ ገዳዩን (ቃየልን) ወለደች፤ እመቤታችን ግን ወሀቤ ሕይወትን ወለደች። ቀዳማዪቷ ሔዋን የወንድሙን ደም የሚያፈስ ልጅን ወለደች፤ ዳግማዪቱ ሔዋን ግን ስለ ወንድሞቹ ደሙን የሚያፈስ

ልጅን ወለደች። የቀዳማይቱ ሔዋን ልጅ (ቃየል) ምድር ተረግማ ኃይልዋን አልሰጥ ስላለችው ከመብላይና ተቅበዝባዥ ኾነ /ዘፍ.፬፥፭-፲፪/፤ የዳግማይቱ ሔዋን ልጅ ግን ያንን ርጋማን አስወገደው በመስቀል ላይም ጠርቆ አስወገደው /ቈላ.፪፥፲፬/። የእመቤታችን ፅንስ አዳምን ያለ ወንድ ዘር ከድንግል ምድር እንደተገኘ ዳግማዊ አዳምም ያለ ዘርዐ ብእሲ በድንግሊቱ ማኅፀን እንደተገኘ ያስተምረናል። ቀዳማዊ አዳም በበደለ ጊዜ ወደ እናቱ ማኅፀን (ወደ ምድር) ተመለሰ፤ ዳግመኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ያልተመለሰው ዳግማዊ አዳም ግን ቀዳማዊውን እንደገና ከእናቱ ማኅፀን እንዲወለድ አደረገው።

- እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከተራራማው ሀገር ወደ ቤቷ በሄደች በተመለሰች ጊዜ የፀነሰችው በግብረ መንፈስ ቅዱስ እንደኾነ ታስረዳው ነበር፤ ነገር ግን ከኅሊናት በላይ ስለኾነበት ነገሩ ረቀቀበት። ፊቷን ሲመለከታት ምንም ዓይነት የውሸት ምልክት አይታይባትም፤ ግን ደግሞ ሆዷ ገፍቷል። በመኾኑም ደግ ነውና ሊገልጥባት አልወደደም። ከዚሁ ጐን ለጐን ግን ከሌላ ወንድ ጋር ተገናኝታለች ብሎ ስላሰበ ወደ ቤቱ ሊወስዳት አልወደደም። በእነዚህ ኹለት ሐሳቦች እየተማታ ወደቤቱ ሊወስዳት እንደማይገባ ግን ደግሞ ነገሩንም ሊገልጥባት እንደማይገባ ወሰነ። ያን ጊዜ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ታየው። በጣም በሚያደንቅ መንገድ መልአኩ “አ ዮሴፍ ወልደ ዳዊት - የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ!” አለው። ይኸውም እግዚአብሔር ለቅድመ አያቱ ለዳዊት “እስመ እምፍሬ ከርሥከ አነብር ዲበ መንበርከ- ከባሕርይህ የተከፈለ ልጅህ ክርስቶስን በዙፋንህ አስቀምጣለሁ” ብሎ የማለለትን ቃል እንዲያስተውስ ነው /መዝ.፻፴፪፥፲፩/። መልአኩ ቀጠለ፤ እንዲህም አለው “ኢትፍራህ ኃሊኦታ ለማርያም ፍኅርትከ እስመ ዘይትወለድ እምኔሃ እመንፈስ ቅዱስ ውእቱ - የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ! ከካህናት እጅ እንደተቀበልህ ከእደ መንፈስ ቅዱስ መቀበልን አትፍራ፤ ከእርሷ የሚወለደው በግብረ መንፈስ ቅዱስ ነውና። ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንድምትወልድ ከረቀቀብህ እነሆ “ናሁ ድንግል ትፀንስ ወትወልድ ወልደ” የሚለውን የነቢዩን ቃል አስታውስ /ኢሳ.፯፥፲፬/። ዳግመኛም ነቢዩ ዳንኤል “ተበትከ ዕብን ዓቢይ እምደብር ዘእንበለ እድ - ታላቅ ደንጊያ እጅ ሳይነካው ከተራራ ወረደ” ብሎ የተናገረውን ልብ በል /ዳን.፪፥፴፭/። ይህ የነቢዩ ዳንኤል ቃል ኢሳይያስ በአንድ ቦታ “ርእይዋ ለኲኩሕ ጽንዕት እንተ ወቀርከሙ ወአዘቅተ ዕምቅተ እንተ ከረይክሙ - ያለዘባችኋትን ጽኑ ዐለት እይዋት የቈፈራችሁትንም ጥልቅ ጕድጓድ አስተውሉ” ብሎ እንደተናገረው ያለ አይደለም ኢሳ.፶፩፥፩/። ምክንያቱም ኢሳይያስ

የወንድና የሴትን ነገር አንሥቶ የተናገረ ሲኾን ነቢዩ ዳንኤል ግን “ዘእንበለ እድ - ያለ እጅ” ነው ያለው። ይኸውም ቀዳማዊ አዳም ለሔዋን አባቷም እናቷም እንደኾነ ኹሉ እመቤታችን ለጌታችን (በተዋሐደው ሥጋ) እናቱም አባቱም ነች።

- ዮሴፍ ዳድቅ ሰው ስለነበረ ነገሩን ሊገልጥባት አልወደደም። ደግነቱም (ጽድቁም) እንደ ሕጉ የኾነ ደግነት አይደለም። ሕጉ እንዲህ ያለ ነገርን ያደረገ ወንድ ወይም ሴት እስኪሞቱ ድረስ በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል ያዝዛልና /ዘዳ.፲፯፡፭፣፯ ፤ ዘዳ.፳፪፡፳፫-፳፬/። ዮሴፍ ግን በስዉር ሊተዋት (ሊለያት) አሰበ እንጂ ሊገልጥባት አላሰበም። ዮሴፍ ይህን የሚደርገው ነገሩ ረቅቆበት፣ ከሚያውቀው የተፈጥሮ ሂደትም ውጪ ስለኾነበት ነው። በመቀጠል የኾነው ኹሉ እግዚአብሔር እንዳደረገው ተገነዘበ። ነገር ግን እንዲህ ያለ ነገር አይቶም ሰምቶም ስለማያውቅ ግራ ተጋባ። በተቃራኒው ደግሞ እመቤታችንን ላለማመን ምንም የማይቻል ነበር። ምክንያም በጣም ብዙ አስረጂ ነገሮችን አስረድታዋለችና። የዘካርያስ ዲዳ መኾን፣ የኤልሳቤጥ መፀነስ፣ የመልአኩ ብሥራት፣ የብላቴናው ዮሐንስ በሐሴት መሞላትና መዝለል፣ የቀደሙ አበው ትንቢት እና ሌሎች ዮሴፍን ለማሳመን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ይነግሩት ነበር። በመኾኑም ነገሩን ሳይገልጥባት በስዉር ሊተዋት (ሊለያት) ወሰነ። እመቤታችን የፀነሰችው በግብረ መንፈስ ቅዱስ መኾኑን ቢያውቅ ኖሮ በስውር ሊተዋት ባላሰበ ነበር።
- የኾነው የተደረገው ኹሉ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ መኾኑን አውቋል። ኾኖም ግን ሌሎች በዙርያ ያሉ ሰዎች ይህን ነገር ሊያምኑት ስለማይችሉ በስውር መተው የተሻለ የጽድቅ ሥራ መስሎ ታየው። ይኸውም በግብር እንዲገናኙት ሳይኾን እንዲያገለግላት፣ እንዲጠብቃት የሰጡት ካህናት ይህን የእግዚአብሔር ሥራ ሊያምኑት እንደማይችሉ ስለሚያውቅ ነው። “የመለኮታዊው ልጅ አባት ነኝ ብል ኃጢአት ነው” በማለት በስውር ሊተዋት አሰበ። ልጇ (ክርስቶስ) በድንግልና የተፀነሰ በድንግልናም የሚወለድ መኾኑን ቢያውቅም ይህን የሚጠረጥሩ ሰዎች እንዳይኖሩ ከእርሷ ተለይቶ መኖርን ፈራ። መልአኩም መጥቶ “ኢትፍራህ ነሢአታ ለማርያም ፍኅርትከ - ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ” አለው። ወንጌላዊው ማቴዎስም ከዚያ በኋላ በጽድቅ በንጽሕና ከእርሱ ጋር እንደኖረች ዮሴፍም እንደወሰዳት ይነግረናል። ለዚህም ነው ካህናት በኋላ ዘመን ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስን እመቤታችን ድንግል ናት ስላለ ወግረው የገደሉት። ዳግመኛም ካህኑ ዘካርያስ ጌታችን እንደተናገረው በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዲገደል ያደረጉት፣ ሕፃናት በሄሮድስ ትዕዛዝ በሚገደሉበት ሰዓት ልጁ ዮሐንስን

በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና ስለሚወለደው ክርስቶስ ምስክር እንዲሰጥ ወደ በረሐ እንዲሸሽ በማድረጉ ነው /ማቴ.፳፫፡፴፭/።

- አንዳንድ ልበ ስሑታን እመቤታችን ጌታን ከወለደች በኋላ ከዮሴፍ ጋር በግብር ተገናኝታለች ሲሉን እንዲህ ብለን እንመልስላቸዋለን፡- “ያቺ ማኅደረ መለኮት የኾነች ድንግል፣ ያቺ መንፈስ ቅዱስ የጸለለባት እመቤት እንደምን ሟች ከኾነ ዕሩቅ ብእሲ ጋር ተመልሳ በግብር ትገናኛለች ተብሎ ይታሰባል? እንደምንስ ዳግም በምጥ በጋር ትወልድ ዘንድ በግብር ተዋውቃለች ተብሎ ይታሰባል? እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሴቶች ኹሉ ተለይታ ንዕድ ክብርት መኾኗን መልአኩ ከተናገረ ከጥንት (ከእናቷ ማኅፀን) አንሥቶ ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ንጽሕት ነበረች ማለት ነው። ይህም ብቻ ሳይኾን በምጥ በጋር ከመውለድ የተለየች ናት ማለት ነው። ስለዚህ እመቤታችን ዳግመኛ ከዮሴፍ ጋር በግብር ተዋውቃ በምጥ በጋር ትወልዳለች ተብሎ ፈጽሞ ሊታሰብ አይገባውም። በሰብአ ትካት ጊዜ ከኖኅ ጋር ወደ መርከብ የገቡ እንስሳት ስንኳ ከግብር የተለዩ ከነበሩ አማኑኤልን በግብር በማኅፀኗ የተሸከመች እመቤታችንማ ፈጽማ እንዲህ በግብር ተዋውቃለች ተብሎ ሊታሰብ አይገባውም። ከመርከቡ ውስጥ ከኖኅ ጋር የነበሩ እንስሳት በግብር ያልተዋወቁት ኖኅ ከልክሏቸው ነው፤ እመቤታችን ግን ከዚህ ግብር የተለየችው በፈቃዷ ነው። በንጽሕና በቅድስና እንደወለደች ኹሉ ንጽሕናዋና ቅድስናዋም እንደዚያ ኾኖ እንዲዘልቅ ፈቃዷ ነበር።
- የአሮን ልጆች እግዚአብሔር ያላዘዘውን እሳት በእግዚአብሔር ፊት በማቅረባቸው በሞት ከተቀጡ /ዘሌ.፲፡፩-፪/ እመቤታችንማ እንዴት? ወይንን የሚነግዱ ሰዎች በወይኑ ላይ ውኃ ቢጨምሩበት ቅጣታቸው የበዛ ከኾነ እምቤታችንማ እንዴት? አንዳንድ ሰዎች የጌታ ወንድሞች ተብለው የሚጠሩ ልጆች ስላሉ እመቤታችን የወለደቻቸው ይመስላቸዋል። ነገር ግን ጌታችንም የዮሴፍ ልጅ መባሉን ሊያስተውሉ ይገባል። ይህም አይሁድ ብቻ ሳይኾን እመቤታችንም እንዲህ አድርጋ ትናገር ነበር። “እስመ ናሁ አቡከኒ ወአነኒ ሠራሕነ እንዘ ነሐሥሠከ- እነሆ አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን” እንዲል /ሉቃ.፪፡፵፰/። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ዮሴፍ እመቤታችንን ወደ ቤቱ እንዲወስዳት የነገረው አንደኛው፡ በሐሰት ሊከሷት የሚችሉትን ሰዎች ጥርጣሬ እንዳይኖራቸው ለማድረግ፤ በተለይ ደግሞ ከመልአኩ ፀንሳ ተገኘች ብለው ሊገድሏት ከሚችሉ ሰዎች ሊጠብቃት ነው። በእነዚህ ሰዎች ዘንድ አንድ የተለመደ ወሬ ነበር። ይኸውም “ድንግል በድንግልና ትወልዳለች፤ ድንግሊቱ በመውለዷ ምክንያትም ከተማይቱ ትጠፋለች፤ ክህነታችን ሀብተ ትንቢታችን

ኹሉ ይወገዳል” የሚል ነው። ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንድምትወልድ የተናገረው ኢሳይያስን በመጋዝ ተርትረው እንዲገደል ያደረጉት ለዚሁ ነበር /ኢሳ.፶፤፲፪/።

- ድንግሊቱ የበኩር ልጇን ወለደችኀ ነገር ግን ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም። ... የበኩር ልጇንም እስክትወልድ ድረስ (ዮሴፍ) በንጽሕና በቅድስና ከእርሷ ጋር ኖረ /ማቴ.፩፥፳፭/። ይህ ቃል የተነገረው ዮሴፍ እመቤታችንን ወደ ቤቱ ከወሰዳት በኋላ ነው። “ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገኀ እጮኛውንም ወሰደ” ብሎ ቀጥሎም “የበኩር ልጇንም እስክትወልድ ድረስ (በግብር) አላወቃትም” እንዲል /ማቴ.፩፥፳፬-፳፭/። በሌላ አገላለጽ ወደ ቤቱ ወሰዳትኀ ነገር ግን በግብር አልተዋወቁም ማለት ነው። ወደ ቤቱ የወሰዳት ከፀነሰች በኋላም ቢኾን እጮኛዋ ስለኾነ ነው። የበኩር ልጇንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ማለትም እንኳንስ በግብር ቀርቶ በሐሳቡም ከእመቤታችን ጋር ሌላ ነገር ለማድረግ አላሰበም ተብሎ ይተረጐማል። እስክትወልድ ድረስ ማለትም ሰዎች እመቤታችን የፀነሰችው በግብረ መንፈስ ቅዱስ እንጂ በዘርዐ ብእሲ እንዳልኾነ እንደተረዱ የሚያስገነዝብ ነው።
- ዳግመኛም የበኩር ልጇንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ማለት ምንም እንኳ እመቤታችንና ዮሴፍ በፈቃዳቸው በንጽሕና በቅድስና ለመኖር ቢያስቡም ጸጋ መንፈስ ቅዱስም ረድቶዋቸዋል ማለት ነው። ጌታችን ከተወለደ በኋላ ያለው ቅድስናቸው ግን የራሳቸው ነጻ ፈቃድ ነው።
- ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በግብር እንዳይተዋወቁ ከልክሎዋቸው እንደነበርና ጌታ ከተወለደ በኋላ ግን በራሳቸው ምርጫ በንጽሕና በቅድስና እንደኖሩ ለመግለጽ “እስከ” በሚለው ቃል ነግሮናል። የበኩር ልጇን እስክትወልድ ድረስ በንጽሕና በቅድስና አብሯት ኖሯል። እንግዲህ እስከ የሚለው ቃል ስለተጠቀሰ ዮሴፍ ከዚያ በኋላ በግብር አውቋታል ተብሎ ድምዳሜ ሊወሰድ ይችላልን? እስከ የሚለው ቃል መጨረሻ የሌለው እስከ ነው። “ጌታ ጌታዬን፡- ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው” ተብሎ ስለተጻፈ /መዝ.፻፱፥፩/ ጌታ ጠላቶቹ በእግሩ መረገጫ ከኾኑ በኋላ ይነሣል ማለት ነውን? ... ከእናንተ መካከል “የጌታችን ወንድሞች እኮ ስማቸው በወንጌል የተጠቀሰ ነው!” የሚለኝ ቢኖር እኔም እንዲህ ብዬ እመልስለታለሁ “ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ሥር ለሚወደው ደቀ መዝሙር (ለዮሐንስ) የሰጣት ስለኾነ እነዚህ ልጆች ልጆቿ እንዳልኾኑ፣ የሴፍም ባሏ እንዳልኾነ ግልጽ ነው” /ዮሐ.፲፱፥፳፯/። እናትና አባትህን አክብር ብሎ ሕግን የሠራ ጌታ እንደምን እመቤታችንን ከልጆቿ አለያይቶ ለዮሐንስ

ይሰጣታል ተብሎ ይታሰባል?” /St. Ephrem the Syrian, Commentary on Tatian’s Diatesaron, pp 60-64/።



- የማይቻለውን ቻልሽ። ምንም ምን የሚወስነው የሌለውን ወሰንሽ። ምልዕተ ክብር ሆይ! በክብረ ወሊድ ላይ ክብረ ድንግልናን ደርበሽ ብትገኚ ላንቺ የተሰጠሽ ክብር ፍጹም ነው። የአካላዊ ቃል ማደሪያ ኾነሻልና፣ ምዕመናንን ሰብስባ የያዘቻቸውና ለሥላሴ ሰጊድን የምታስተምሪላቸው (አንድነት ሦስትነት በጐላ በተረዳ ነገር የታወቀብሽ) ጴጥሮስ በናሕሰ ኢዮጴ ያያት የቤተ ወንጌል ሰፊ መጋኛ አንቺ ነሽ /ሐዋ.፲፥፱-፲፮/። ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ አባ ጊዮርጊሥ ዘጋሥጫም፡- “ሰላም ለኪ መንጦላዕተ ገርዜን - የበፍታ መጋረጃ ሰላምታ ለአንቺ ይገባል” ብሏል /የአባ ጊዮርጊሥ የሰባቱ ጊዜያት የሃይማኖትና የጸሎት መጽሐፍ ትርጓሜ በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ፣ ገጽ ፪፭/።
- ሙሴ ያየውን ዓምደ እሳት የተሸከምሽ አንቺ ነሽ /ዘጸ.፲፫፡፳፪/። ይኸውም ዓምደ እሳት ያልኩት ሰው ኾኖ በማኅፀንሽ ያደረው ወልደ እግዚአብሔር ነው። ሰማይና ምድር ለፈጠረ ለእርሱ ማደሪያ ኾንሽው። ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማኅፀንሽ ቻልሽው። ሰማይና ምድር የማይወስኑትን ለመወሰን የታመንሽ ነሽ። ከምድር ወደ ሰማይ ለመውጣት መሰላል ኾንሽ። በመሰላል የላዩ ወደ ታች ይወርዱበታል፤ የታቹ ወደ ላይ ይወጡበታል። የላዩ ወደታች እንዲወርዱበት መለኮትም ከአንቺ ትስብእትን ተዋሕዷል፤ የታቹ ወደ ላይ እንዲወጡበትም ትስብእት ከመለኮት ጋራ ለመዋሐዱ ምክንያት ኾነሻል። ድንግል ሆይ! ክብርሽ ከፀሐይ ብርሃን ይበልጣል። ቅዱሳን፣ ሰብአ ሰገል /ማቴ.፪፡፪/፣ እነ በለዓም /ዘኅ.፳፬፡፲፯/፣ ሐዋርያት ደስ ብሏቸው ያዩት ኮከብ ካንቺ የተወለደ ምሥራቅ አንቺ

ነሽ። ይኸውም በግር፣ በጋር፣ በምጥ ትወልድ ዘንድ በሔዋን የፈረደባት ነው። አንቺ ግን ምልዕተ ክብር ሆይ! ደስ ይበልሽ የሚል ድምፅ ሰማሽ /ሉቃ.፩፡፳፰/። ሔዋን "በሕማም ለዲ" የሚል ድምፅ ሰምታ /ዘፍ.፫፡፲፮/ ምክንያተ ሞት ቃየልን አስገኘች /ዘፍ.፬፡፩-፭/። አንቺ ግን "ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ" የሚል ደምፅ ሰምተሽ ፍጥረትን ኹሉ የሚገዛ ንጉሥን ወለድሽልን /ሉቃ.፩፡፴፩/። ሄሬኔዎስ የተባለ ሊቅም ይህንን አንቀጽ በረጐመበት ድርሳኑ እንዲህ ብሏል፡- "እነሆ ጌታ የራሱ ወደኾኑት በግልጥ (በለቢሰ ሥጋ) መጣ። ትእዛዙን ተላልፎ በዕፅ የሞተውን አዳም በዕፅ (በመስቀል) ላይ ታዝዘና ካሣውን ከፍሎ፣ ወደ ጥንተ ተፈጥሮው ይመልሰው ዘንድ በራሱ ጥበብ ከፍጥረቱ ተወለደ። ለአንድ ወንድ የታጨችው ድንግል በምክረ ከይሲ ያመጣችውን ያለመታዘዝ ኃይል የእውነት መልአክ ለአንድ ወንድ ለታጨችው ድንግል ባበሠራት ጊዜ ፈራረሰ። ቀዳማይቱ ሔዋን ከእግዚአብሔር እንድትርቅና ቃሉን እንድትቃወም በክፉ መልአክ እንደተታለለች ኹሉ፣ ዳግማይቱ ሔዋን ቅድስት ድንግል ማርያምም ደጉ መልአክ ይዞት የመጣው መልካሙን ዜና እንድትቀበለውና እግዚአብሔርን በከዊነ ቃሉ እንደምትወልደው አመነች። ቀዳማይቱ ሔዋን እግዚአብሔርን እንዳትታዘዘው ክፉ መልአክ አታለላት፤ ወደቀችም። ዳግማይቱ ሔዋን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን እግዚአብሔርን እንድትታዘዝ ቅዱስ መልአክ አሳመናት፤ እርሷም ሔዋንን ረዳቻት። ነገደ አዳም በአንዲት ድንግል አለመታዘዝ ምክንያት ሞት ተፈረደበት፣ ኾኖም በሌላይቱ ድንግል መታዘዝ ምክንያት ዳነ። የፍጥረት በኩር የሚኾን አዳም የበደለው በደል የእግዚአብሔር በኩር በሚኾን በወልደ እግዚአብሔር መቀጣት ተፈወሰ። የእባቡ ተንኰል በርግቡ የዋኅነት ተዋጠ፤ ለሞት ሲዳርገን የነበረው ቁራኝነትም ተሰበረ።"

- ሰው ኾኖ ያዳነን መሐሪ ነው፤ ሰው ወዳጅ ነው። ድንግል ሆይ! በእንተዝ ንዌድስኪ - ስለዚህ ነገር መልአኩ "ቡርክት አንቲ እም አንስት" ብሎ እንዳመሰገነሽ እኛም "ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ- እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍሽ ነስቶ ካንቺ ጋራ አንድ ባሕርይ ኹኗልና (ተፈሥሒ) ደስ ይበልሽ" ብለን እናመሰግንሻለን። እንዲህ ካለ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታቸን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ይኽን ሲጨርስ በያዘችው መስቀለ ብርሃን ባርካው ታርጋለች። እርሱም እጅ ነሥቶ ይቀራል።
- አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን።

የቅዳሜ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ

ገ/እግዚአብሔር ኪደ

- **(መቅረዝ ዘተዋሕዶ ነሐሴ ፲፭ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.)፡-** በዚህም ቀን እመቤታችን ትመጣለችኍ የብርሃን ድባብ ይዘረጋልኍ የብርሃን ዙፋን ይነጠፋል። ከዚያ ላይ ኾናም ሊቁን ባርካው ምስጋናዉን ጀምሯል።
- ፩. ንጽሕት ነሽኍ ብርህት ነሽ። በአፍአ በውስጥ ንጽሕት ነሽ። ሊቁ "ዲያቲሳሮን" በተባለው የወንጌል ትርጓሜ መጽሐፉ የእመቤታችንን ንጽሕና ሲናገር፡- "የማርያም ሰውነት የምድር ላይ መቅደስ ነው። በዚሁ መቅደስም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በጎጢአት፣ በሞትና በርግማን ፈንታ የበረከትን ዘር ሊዘራ መጣ። የኤልሳቤጥም ሰላምታ ይህንን አረጋገጠ።... አንተና እናትህ ብቻ በማንኛውም ረገድ ንጹሐን ናችሁ። ጌታ ሆይ! በአንተ ውስጥ ምንም ነቅዕ የለምኍ በእናትህም ውስጥ ምንም ምልክት የለም" ብሏል /St. Ephrem the Syrian, Commentary on Tatian's Diatesaron, pp 91-92/።
-
- ጌታን በማኽል እጅሽ የያዝሽው ሆይ! ምልዕተ ክብር ሆይ! (ተፈስሒ) ደስ ይበልሽ እያሉ ፍጥረት ኹሉ ከአንቺ ጋር ደስ ይላቸዋል። እግዚአብሔር ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ከአንቺ ጋር አንድ ባሕርይ ቢኾን ባለሟልነትን አግኝተሻልና (ተፈስሒ) ደስ ይበልሽ። ግርምት ድንግል ሆይ! ክብርሽን ገናንነትሽን ዕፁብ ዕፁብ እያልን እናመሰግናለን (እናደንቃለን)። ከማኅፀንሽ ፍሬ የባሕርያችን ድኅነት ተገኝቷልና ከመልአኩ ጋር እንደ መልአኩ ምስጋና እናቀርባለን። የማኅፀንሽ ፍሬ ከአባቱ ጋር አስታርቆናልና እንደ መልአኩ ምስጋና እናቀርብልሻለን። ሊቁ ቅድም በጠቀስነው መጽሐፉ፡- "... መልአኩ ወደ አንዲት ድንግል ተላከ። ወደ እርሷ ገብቶም "እነሆ ድንግልናሽ ሳይነካወጽ ትፀንሻለሽኍ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽኍ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ" አላት/ሉቃ.፩፡፴፩//። ይኸውም በሥጋ ተገልጦ ሊመጣ ስላለው ስለ አካላዊ ቃል ሲናገር ነው። ሲነግራት "ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ" አላት እንጂ "ኢየሱስ የተባለው" እንዳላላት ልብ በሉ። ይኸውም የሰው ልጆች ወልደ እግዚአብሔር በለበሰው ሥጋ የሚድኑበት ስም መኾኑን የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም ኢየሱስ ማለት በዕብራይስጥ "መድኅን" ማለት ነውና። መልአኩ "ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ" ሲላት መድኅን

ትዩዋለሽ ማለቱ ነው። ለምን? ሕዝቡን ኹሉ ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና" ብሏል /ማቴ.፩፡፳፩/። ከአባቱ ጋር ካስታረቀን ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

- ፪. አባ ሕርያቆስ፡- "እግዚአብሔር አብ በሰማይ ኾኖ ምሥራቅንና ምዕራብን ሰሜንና ደቡብን ዳርቻዎችንም ኹሉ በእውነት ተመለከተ፤ እንደ አንቺ ያለ አላገኘም። የአንቺን መዓዛ ወደደ፤ የሚወደው ልጁንም ወደ አንቺ ሰደደ" እንዲል /ቅዳ.ማር. ቁ.፳፱/ እንደ ሰርግ ቤት አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ ኾነሽ ቢያገኝሽ መንፈስ ቅዱስ አድሮብሻልና፤ ኃይለ ልዑል ወልድም ሥጋሽን ለብሷልና አንድም መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ ግብራት ከልክሎሻልና ኃይለ ልዑል ወልድም ከሦስቱ ግብራት ከልሎሻልና ለዘለዓለሙ ጸንቶ የሚኖር አካላዊ ቃልን ወለድሽልን /ሃይ.አበ.፪፲፡፳፱/። ሰው ኾኖ ከኃጢአት አዳነን /ማቴ.፩፡፳፩/። ሰው ኾኖ ከኃጢአታችን ፍዳ ካዳነን ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፫. መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በሥጋ ወልደሽልናልና ከዳዊት ሥር የተገኘሽ ባሕርይ አንቺ ነሽ /ሉቃ.፩፡፴፪/። ቅድመ ዓለም የነበረ፣ ከአብ ባሕርይ ዘእም ባሕርይ አካል ዘእም አካል የተወለደ፣ ተቀዳሚ ተከታይ (ታላቅም ታናሽም) የሌለው አካላዊ ቃል ባሕርዩን በሥጋ ሠወረ። ከአንቺም አርአያ ገብርን ነሣ /ፊል.፪፡፯/።
- ከእናንተ መካከል፡- "አካላዊ ቃል አርአያ ገብርን ነሥቶ (የባሪያን መልክ ይዞ) በሰውም ምሳሌ ኾኖ ራሱን ባዶ አደረገ ሲል ምን ማለት ነው?" ብሎ የሚጠይቅ ሊኖር ይችላል። እኛም እንዲህ ብለን እንመልስለታለን፡- ራሱን ባዶ አደረገ ሲል የእኛን ባሕርይ ገንዘብ ባደረገ ጊዜ ባሕርየ መለኮቱ ተለውጧል ማለት አይደለም። ባሕርየ መለኮቱን ትቶ መጣ ማለትም አይደለም፤ በፈቃዱ ደካማ ባሕርያችንን ገንዘብ አደረገ ማለት ነው እንጂ። ወልደ እግዚአብሔር ራሱን ባዶ ያደረገው በመቅድመ ወንጌል "ከጥንት ዝምሮ በባሕርያችን እስኪሠለጥን ድረስ ሰይጣን በተንኰል በሥጋ ከይሲ እንደተሠወረ፤ እኛም ከፍዳ መዳናችን ቃለ እግዚአብሔር በባሕርያችን በመሠወሩ ኾነ" ተብሎ እንደተጻፈ የእኛን ባዶነት በጸጋው ለመሙላት ነው። ሰው የኾነው እኛን አማልክት ዘበጸጋ ያደርገን ዘንድ ነው።" የባሪያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ኾኖ ስለ እኛ ብሎ ራሱን ባዶ ካደረገ ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፬. አደፍ ጉድፍ ሳይኖርብሽ አምልክን የወለድሽው እመቤታችን ሆይ! በኃጢአት ብርድ የተያዘውን ዓለም ኃጢአቱን ያርቅለት ዘንድ ፀሐየ ጽድቅ ጌታ ከአንቺ ተወልዷልና፤ ነቢያት ይወርዳል ይወለዳል

ብለው እንደተናገሩም ዘር ምክንያት ሳይኾንሽ፣ መለወጥ ሳያገኝሽ ወልደሽዋልና ከምድር በላይ ያለሽ ኹለተኛ ሰማይ አንቺ ነሽ። ኢትዮጲያዊው ቄርሎስም፡- “ኦ ሰማይ ዳግሚት ዘወለደቶ ለፀሐየ ጽድቅ ዘውእቱ ብርሃነ ቅዱሳን ዘሰደዶ ለጽልመት - ጨለማን ያሳደደውን (ያስወገደውን) የቅዱሳን ብርሃን የሚኾን አማናዊ ፀሐይን የወለደች ኹለተኛይቱ ሰማይ ሆይ! ...” እያለ ያወድሳታል /አርጋኖን ዘረቡዕ/። ዘር ምክንያት ሳይኾንሽ ከወለድሽው ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።



-
- ፭. ከተለዩ የተለየሽ፣ ከከበሩ የከበርሽ በውስጧም ሕግ የተጻፈበት ኪዳን ያለብሽ የተሠወረ መና ያለበት መሶበ ወርቅ ያለብሽ ደብተራ (ድንኳን) አንቺ ነሽ /ዘጸ.፳፭፡፩-፴/። ይኸውም መና የተባለው ሰው ኾኖ በማኅፀንሽ ያደረው ወልደ እግዚአብሔር ነው። መተርጒማኑ ይህን የበለጠ ሲያብራሩት፡- “ድንኳኗ የእመቤታችን ምሳሌ፤ ቅድስት የነፍሷ፤ ቅዱሳን የሥጋዋ፤ ታቦቱ የመንፈስ ቅዱስ፤ ጽላት የልቡናዋ፤ ቃሉ በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸላት ምሥጢር ምሳሌ ነው። አንድም ቅዱሳን የሥጋዋና የነፍሷ፤ ቅድስት የልቡናዋ፤ ታቦት የማኅፀኗ፤ ጽላት የትስብእትዋ፤ ቃሉም የመለኮት ምሳሌ ነው” ይላሉ /ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፣ ገጽ ፻፹፬/። ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በአርጋኖን ዘሐሙስ ላይ፡- “ተፈሥሒ ኦ ደብተራ ብርሃን ማኅደሩ ለዐቢይ ሊቀ ካህናት - የታላቁ ሊቀ ካህናት ማደርያ የብርሃን ድንኳን ሆይ! ደስ ይበልሽ” በማለት የሊቀ ካህናት የባሕርይ አምላክ የክርስቶስ እናት አማናዊት ድንኳን መኾኗን አስተምሯል።

- አካላዊ ቃል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው ኾነ። የክብር ባለቤት እርሱን በዚህ ዓለም ወለደችው። ለዘለዓለሙ ጸንቶ የሚኖር አካላዊ ቃል ሰው ኾኖ ከኃጢአታችን ፍዳ አድኖናልና ሰው ኾኖ ያዳነን የነባቢ በግዕ (የሚናገር በግ የክርስቶስ) እናቱ ደስ ይላታል /ዮሐ.፩፥፳፱/። ለዘለዓለሙ ጸንቶ የሚኖር አካላዊ ቃል ሰው ኾኖ ከኃጢአታችን ፍዳ ካዳነን ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፯. እርሱን ከወለድሽ በኋላ ማኅተመ ድንግልናሽ ሳይለወጥ ኦረሻልና የክርስቶስ እናቱ ተባልሽ። ድንቅ በሚያሰኝ ተዋሕዶ አማኑኤልን ወልደሽዋልና ባለመለወጥ አጸናሽ። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን መምህር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ለማንም ሴት ያልተሰጠ ለድንግል ማርያም ብቻ የተሰጠ ድንግልና ከእናትነት ጋር አስተባብራ ስለ መገኘቷ ሲገልጥ "ወሰቦሂ ወለደቶ ዐቀበ ድንግልና፣ ዘእንበለ ርኩስ ከመ በፀንሳ መንክር ትኩን መራሂተ ለሃይማኖት ዐባይ - ከድንግል ተወለደ፤ በወለደችውም ጊዜ ድንግልናዋ ያለመለወጥ አጸና። ድንቅ የሚኾን ፅንሷ ለደገኛው ሃይማኖት መሪ ትኾን ዘንድ" በማለት ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን ስትወልድው ማኅተመ ድንግልናዋ እንዳልተለወጠ ጌታም ሰው ሲኾን ባሕርየ መለኮቱ ላለመለወጡ፣ እርሷ ድንግል ወእም (ድንግልም እናትም) ስትባል እንደምትኖር አካላዊ ቃል ክርስቶስም አምላክ ወሰብእ (ሰው የኾነ አምላክ) ሲባል የሚኖር የመኾኑን የተዋሕዶ ልዩ ምሥጢርን ያወቅንባት የተረዳንባት እርሷ ብቻ መኾኗን አስተምሯል /ሃይ.አበ.፶፯፥፶፪/። እንዲህ ካለ ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፯. ከምድር እስከ ሰማይ ደርሳ፣ በላይዋ ዙፋን ተነጽፎባት፣ በዚያ ላይ ንጉሥ ተቀምጦባት፣ መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ያዕቆብ በፍኖት ሎዛ ያያት የወርቅ መሰላል አንቺ ነሽ /ዘፍ.፳፰፥፲-፳፪/። ሰው ከመኾኑ አስቀድሞ ሰውም ከኾነ በኋላ የማይመረመር እርሱን በተፈትሖ በማይታወቅ በማኅፀንሽ ችለሽዋልና እኛን ስለማዳን ከአንቺ ሰው ከኾነ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ሰዋስው (አማላጅ) ኾንሽን። እኛን ስለማዳን ከአንቺ ሰው ከኾነ ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፰. ጽርሐ ንጽሕት ሆይ! እነሆ ጌታ የፈጠረውን ዓለም ኹሉ በቸርነቱ ብዛት ያድን ዘንድ ከአንቺ ተወለደ። ቸር ሰው ወዳጅ ነውና በአፍአ በውስጥ እናመሰግነው። ቸር ሰው ወዳጅ ከኾነ ልጅሽ ፅንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

- ፱. አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ ድንግል ምልዕተ ክብር ሆይ! ደስ ይበልሽ። ከእናትሽ ማኅፀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ጠብቆሻልና የዓለም ኹሉ መክበሪያ ንጽሕት ጽዋዕ ነሽ (ከሥላሴ ለምንጠጣው ክብር ምክንያት አንቺ ነሽ)።
- እንደ ደብተራ ኦሪቷ ማለትም ሙሴና አሮን በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት አብርተው በቀዳማይ ሰዓተ መዓልት እንደሚያጠፏት ፋና ያይደለሽ የማትጠፊ ፋና ነሽ /ዘጸ.፳፭፡፴፩-፴/።
- እንደ ቀደመችው የኦሪት ቤተ መቅደስ ያይደለሽ የማትፈርሺ መቅደስ ነሽ /፩ኛ ነገ.፮፡፴፭-፶/። ሊቁ አባ ጊዮርጊሥ ዘጋሥጫም፡- "አንቲ ውእቱ መቅደስ ዘሐነጸ ሰሎሞን ወአስቀጸላ በሜላትሮን ወለበጠ ዳቤራ በውሳጥያተ መቅደስ ... - ሰሎሞን ያሠራት እንደ ዝናር እንደ ዐምድ ባለ ወርቅ የጠፈሯን ዙርያ ያስጌጣትን በመቅደስ ውስጥ ያለቺውን ቅድስተ ቅዱሳንዋን ዐውደ ምሕረቷን ግድግዳዋን በጥሩ ወርቅ ያስጌጣትን ቁመቱ ሃያ ክንድን ክንፉ ዐሥራ አምስት ክንድ የሚኾን ኪሩብን በውስጧ ያሣለባት ቤተ መቅደስ አንቺ ነሽ" በማለት በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች እመቤታችን ሰሎሞን ባሠራት የወርቅ ቤተ መቅደስ መስሎ ኹለንተናዋ በንጽሕና በቅድስና ያጌጠች የተዋበች መኾኗን አስተምሯል /አርጋኖን ዘወርብ/። ዳሩ ግን እመቤታችን በንጽሕናዋ በቅድስናዋ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ብትመሰልም ሊቁ (ኤፍሬም) እንዳለው ክብሯ የላቀ ነው፤ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናትና የማትፈርስ መቅደስ ናት /መዝ.፹፮፡፩-፭/።
- የማትለወጥ የቅዱሳን ሃይማኖታቸው (ቅዱሳን የሚያምኑበት ክርስቶስን የወለድሽላቸው አንቺ) ነሽ። ድንግል ሆይ! በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ ይቅር ይለን ዘንድ፣ ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ከልጅሽ ዘንድ አማልጅን። ኃጢአታችንን ከሚያስተሠርይልን ልጅሽ ዕንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳያነሣን ለምኚልን።
- አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው አሜን!!!

የእሑድ ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ

ገ/እግዚአብሔር ኪደ

- **(መቅረዝ ዘተዋሕዶ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፳፻፭ ዓ.ም.)፡-** በዚህ ዕለት እመቤታችን ከወትሮው ይልቅ ቀደም ብላ መጥታለች። "ዛቲ ዕለት ተዓቢ እምኩሎን ዕለታትን፤ ወውዳሲያቲሃኒ የዓብያ እምኩሉ ውዳሴያት - ከዕለታት ኹሉ ይህቺ ዕለት ታላቅ ናት፤ ከውዳሲያቱም ኹሉ የዚች ዕለት ውዳሴ ታላቅ

ነው" አለችውና ባረከችው። እርሱም በቤተ መቅደስ ባሉ ንዋያት ማለትም፦ በመሶበ ወርቅ፣ በተቅዋመ ወርቅ፣ በማዕጠንተ ወርቅ፣ በበትረ አሮን እየመሰለ ሲያመሰግናት አድሯል።

- ፯. ንዕድ ክብርት ሆይ! ከሴቶች ተለይተሽ የሥላሴ ባለሟል ተባልሽ። ከተለዩ የተለየሽ፣ ከከበሩ የከበርሽ፣ ቅዱሳን ኪሩቤል የተሣለብሽ፣ ቅዱሳን ካህናት የሚያመሰግኑሽ ኹለተኛ ክፍል አንቺ ነሽ /ዘጸ.፳፯፡፩-፴/።
- ሕግ የተጻፈባት ጽላት ያለብሽ የምትባዪ አንቺ ነሽ /ዘጸ.፴፪፡፲፭-፲፱/። ኪዳንም ያልኹት በእግዚአብሔር ጣቶች የተጻፉ (በግብር አምላካዊ የተገኙ) ዐሥሩ ቃላት ናቸው። ዐሥርቱ ቃላትን በጽላቱ ጽፎ እንዳኖረ ኹሉ ዋሕድ ቃለ እግዚአብሔርም በአፃብዐ መንፈስ ቅዱስ (ያለ ወንድ ዘር፣ በግብረ መንፈስ ቅዱስ) በማኅፀንሽ እንዲቀረጽ ኾኗልና የሙሴ ጽላት አንቺ ነሽ /ቅዳ.ማር. ቁ.፴፫/። ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብም በነገረ ማርያም መጽሐፉ፦ "... ወማኅፀናሰ ለማርያም ድንግል በክልኤ ይትሜሰል በጽላት ዘተጽሕፈ ውስቴታ ዐሠርተ ቃላት። ወዐሠርተ ቃላት ቀዳሜ ስሙ ለወልዳ ውእቱ ዘውእቱ የውጣ ዘተሰምየ በኍልቁ ዐሠርተ ቃላት - ... በኹለት ወገን ድንግል የምትኾን የማርያም ማኅፀንስ ዐሥሩ ቃላት በውስጧ በተጻፈ ጽላት ይመሰላል። ዐሥሩ ቃላትም የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስ የመዠመርያ ስሙ ነው፤ ያውም የውጣ በዐሥሩ ቃላት የተጠራ ነው" ብሏል /ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን፣ ክፍል ፭፣ ገጽ ፻፶፭፣ በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ/።
- ከአንቺ ሳይለወጥ ሰው ኾነን። ለኦሪት ሳይኾን ለወንጌል ሊቀ ካህናት ኾነን። ለምድረ ርስት ሳይኾን ለመንግሥተ ሰማያት አስታራቂ ኾነን። ሐዋርያው ጳውሎስ፦ "በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘንን፤ እርሱም የበደላችን ስርየት ነው" እንዲል በከበረ ደሙ ፈሳሽነት በዓለመ ሥጋ በዓለመ ነፍስ ያሉትን አዳናቸው /ኤፌ.፩፡፯/። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም የኤፌሶንን መልእት በተረጐመበት በአንደኛው ድርሳኑ ላይ፦ "ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኘነው ሥርየተ ኃጢአት በርግጥ ታላቅ ነው። ተቀዳሚ ተከታይ በሌለው በልጁ ደም መኾኑ ግን ከምንም በላይ ታላቅ ነው" በማለት የእግዚአብሔር ከኅሊናት የሚያልፈውን የማዳን ምሥጢር (ፍቅር) በመደነቅ ተናግሯል።
- በከበረ ደሙ ፈሳሽነት በዓለመ ሥጋ በዓለመ ነፍስ ያሉትን ካዳነ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ከብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

- ፪. ኹል ጊዜ ንጽሕት የምትኾኚ አምላክን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ! ስለዚህ ነገር ኹላችን እናከብርሻለን፤ እናገንሻለንም። ሰውን ከሚወድ ሰው ከሚወደው ከርሱ ይቅርታን እናገኝ ዘንድ ኹል ጊዜ ዓይነ ልቦናችንን ወዳንቺ እንሰቅላለን።
- ሽምሽር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ (በአምልኮተ ጣዖት ከማይለወጥ) እንጨት የተቀረጸ በአፍአ በውስጥ በወርቅ የተለበጠ ታቦት አካላዊ ቃልን ይመስልልናል /ዘጸ.፳፭፡፱-፳/። ይህ ንጹሕ የሚኾን፣ መለወጥ የሌለበት እርሱ ባለመለወጡ አለመለወጧን ነገራት፤ ከአብ ዕሪና ባለመለየቱም አለማለየቷን ነገራት (አምላክ ወሰብእ ኾኖ እርሷም እም ወድንግል መኾኗን ነገራት)። ከጥበብ በሚበልጥ ጥበብም ዘር ምክንያት ሳይኾነው እንደ እኛ ሰው ኾነ። አበው፡- “ዓለሙን ከፈጠረበት ጥበብ ይልቅ ሰው ኾኖ ዓለሙን ያዳነበት ጥበብ ይበልጣል” የሚሉትም ስለዚሁ ነው። አደፍ ጉድፍ ሳያገኝሽ መለኮቱን አዋሕዶ ከሥጋሽ ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ነሥቶ ሰው ኾነ። መለኮቱን አዋሕዶ ሰው ከኾነ ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኝልን።
- ፫. እግዚአብሔር በፈጠራቸው በኪሩቤል አምሳል፤ ሙሴ የሣላቸው ኪሩቤል የሚጋርዱሽ መቅደሰ ሙሴ አንቺ ነሽ። አንድም እግዚአብሔር በፈጠራቸው በኪሩቤል አምሳል፣ ሰሎሞን የሣላቸው ኪሩቤል የሚጋርዱሽ መቅደሰ ሰሎሞን አንቺ ነሽ። ጌታ በማኅፀንሽ ያደረብሽ አማናዊቷ መቅደስ አንቺ ነሽ። ሳይለወጥ ካንቺ ሰው የኾነው አካላዊ ቃል በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ ኃጢአታችንን የሚያስተሠርይልን ኾነ። ኃጢአታችንን ከሚያስተሠርይልን ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኝልን።



- ፱. መና ያለብሽ መሶበ ወርቅ አንቺ ነሽ /ዘጸ.፲፮፡፴፫-፴፬/። ይኸውም መና የተባለው ከሰማይ የወረደና ፱ ወር ከ፮ ቀን በማኅፀንሽ የተሸከምሽው ነው። እርሱም "አበዊክሙሰ መና በልዑ በገዳም ወሞቱ - አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ፤ ሞቱም" እንዳለው ያይደለ፤ ይልቁንም ለሰው ኹሉ ሕይወት የሚያድል ኅብስት ነው /ዮሐ.፮፡፶/። ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በአንቀጸ ብርሃን ላይ፡- "አስተማሰልናኪ ቅድስት ወብፅዕት ስብሕት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት በመሶበ ወርቅ ዘውስቴታ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ወሃቤ ሕይወት ለኵሉ ዘየአምን ኪያሁ ወይበልዕ እምኔሁ በአሚን ወበልብ ሥሙር ምስለ እለ በየማኑ - የተለየሽና ደግ የኾንሽ የተመሰገንሽና የተባረክሽ የከበርሽና ከፍ ከፍ ያልሽ ሆይ! የሕይወት ኅብስት ባለበት በወርቅ መሶብ መሰልንሽ። የሕይወት ኅብስትም በቀኙ ካሉ ጻድቃን ጋር እርሱን ለሚያምን በሃይማኖትና ፈቃደኛ በኾነ ልብ ከእርሱ ለሚበላም ኹሉ ሕይወትን የሚሰጥ ከሰማይ የወረደ ነው" ብሏል /ቁ.፶/። ዳግመኛም አባ ጊዮርጊሥ ዘጋሥጫ፡- ኦ መሶብ ቤተ ልሔማዊት ዘወለደቶ ለኅብስተ ሰማይ ዘኢያብቋልዎ ዝናማት ወዘኢሐፀንዎ አየራት - ዝናማት ያላበቀሉትን አየራት ያላሳደጉትን የሰማዩን እንጀራ የወለድሽው ቤተ ልሔማዊት መሶብ ሆይ" በማለት መስክሯል /አርጋኖን ዘረቡዕ/። ከአባቶች አንዱም፡- "ድንግል ሆይ! በእውነቱ አንቺ ከታላላቅ ይልቅ ታላቅ ነሽ። ማኅደረ ቃለ አብ ሆይ! አንቺን ሊተካከል የሚችል ታላቅ ማን ነው? ድንግል ሆይ! ከየትኛው ፍጥረት ጋር አወዳድርሻለሁ? አንቺ ቀድሞ በወርቅ ካጌጠችው የሕጉ ታቦት ይልቅ በንጽሕና ያጌጥሽ ታላቅ ነሽ! እውነተኛውን መና የተሸከምሽ መሶበ ወርቅ አንቺ ነሽ። መና

የተባለውም መለኮት የተዋሐደው ሥጋው ነው" ብሏል። ኅብስተ ሕይወት ከሚባል ልጅሽ ጸንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

- ፭. ብርሃንነት ያለውን ፋና የተሸከምሽ የወርቅ ተቅዋም (መቅረዝ) አንቺ ነሽ /ዘጸ.፳፭፡፴፯-፴/። ይኸውም ፋና ለሰው ኹሉ ዕውቀትን የሚገልጽ ብርሃን ነው። ጥንት ከሌለው ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው። ከባሕርይ አምላክ የተገኘ የባሕርይ አምላክ ነው። ሳይለወጥ ካንቺ ሰው የኾነው ነው። ሰውም በመኾኑም በድንቁርና በቀቢጸ ተስፋ ለምንኖር ለኛ አበራልን (ዕውቀትን ገልጸልን)። በጥበቡ ባደረገው ሥጋዊ እግረ ልቡናችንን ወደ ሕገ ወንጌል ጎዳና አቀናልን /ኢሳ.፱፡፩-፪፣ ማቴ.፬፡፲፬-፲፯/። ታላቁ የዜማ አባት ሊቁ ቅዱስ ያሬድም፡- "አንቲ ውእቱ ተቅዋም ዘወርቅ ዘኢገብራ እደ ኬንያ ዘሰብእ... - የብልሐተኛ እጅ ያልሠራት በውስጧም መብራት የሚያበሩባት የወርቅ መቅረዝ አንቺ ነሽ፤ ራሱ የአብ ብርሃን ያበራባታል እንጂ። ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ወደ አንቺ መጥቶ አደረ። አምላክነቱም በዓለም ኹሉ አበራ። ጨለማን ከሰዎች ላይ አራቀ። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ በብርሃኔ እመኑ፤ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ ብሎ በሚያድን ቃሉ አዳነን" ብሏል /ቁ.፰፣ ዮሐ.፲፪፡፴፮፣ ፭ኛ ዮሐ.፩፡፭/። በጥበቡ ባደረገው ሥጋዊ እግረ ልቡናችንን ወደ ሕገ ወንጌል ጎዳና ከአቀናልን ልጅሽ ጸንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፮. ቡሩክ አሮን ከቤተ መቅደስ ይዞሽ የወጣ እሳትነት ያለውን ፍሕም የተሸከምሽ ማዕጠንተ ወርቅ አንቺ ነሽ /ዘጸ.፴፡፮-፰/። ፍሕም የተባለውም በአፍኣ በውስጥ በሥጋ በነፍስ ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ነው። ይኸውም ከአንቺ ሰው የኾነውና "ወአንከረ አብ እምዝንቱ መሥዋዕት - ከዚህ መሥዋዕት የተነሣ አብ አደነቀ" እንዲል /ሃይ.አበ.፰፰፡፳፫/ ለአባቱ ራሱን ያማረ የተወደደ መሥዋዕት አድረጎ ያቀረበ አካላዊ ቃል ነው /ኤፌ.፭፡፪/። ራሱን ያማረ የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ካቀረበ ልጅሽ ጸንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፯. አካላዊ ቃልን የወለድሽልን መልካም ርግብ ማርያም ሆይ! ደስ ይበልሽ። ከእሴይ ሥር የወጣሽ መዓዛ ሠናይ አበባ አንቺ ነሽ። መዐዛ ሰናይ የተባለውም የቅዱሳን መዐዛ የሚኾን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው /መጽሐፈ ድጓ፣ ገጽ.፻፯፱/። መዐዛ ሠናይ ከተባለ ልጅሽ ጸንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።
- ፰. ሳይተክሏት የበቀለች፣ ውሃ ሳያጠጧትም የለመለመች ያበበች ፲፪ በኩረ ሎሚ ያፈራች የአሮን በትር ነበረች /ዘኁ.፲፯፡፰-፲/። ከቤተ መቅደስ ፲፪ ዓመት ኑረሽ፣ ዘር ምክንያት ሳይኾነው ሰው ኾኖ

ያዳነን እውነተኛ አምላካችንን ክርስቶስን የወለድሽልን አንቺም እንደርሷ ነሽ /ኢሳ.፯፡፲፬/። አባ ጊዮርጊሥ ዘጋሥጫም በአርጋኖን ዘሰኑይ ላይ፡- "ዕፀ ከርካዕ እንከ እሰምየኪ እስመ ከርካዕ ሠናየ ይጸጊ፤ ወሠናየ ይፈሪ፤ ወሠናየ ይጼኑ፤ ወከመ በትር ይቡስ ዘቦ ላዕሌሁ ወፅአ ዑፃዌ ክህነት አሥረጸ አዕጹቀ ወአቍጸለ ከርካዕ ምዑዘ፤ ወከማሁ አንቲኒ ነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ ዐሠርተ ወክልኤተ ክራማተ ወፀነስኪዮ ለኢሱስ ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ - እንግዲህ የሎሚ ዕንጨት ብዬ እጠራሻለሁ። ሎሚ መልካሙን ያብባል፤ መልካሙን ፍሬ ያፈራል። በጐ በጐ ይሸታልና ዕጣ እንደ ወጣበት ደረቅ በትር ሳይተከል በቤተ መቅደስ ለምልሞ፣ ቅንጣት አውጥቶ፣ አብቦ ተገኘ። ሽታው ያማረ የተወደደውን ሎሚ አፈራ። እንዲሁም አንቺ በቤተ መቅደስ ዐሥራ ኹለት ዓመት ተቀምጠሽ ያለ ወንድ ዘር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፀነስሺው" በማለት አብራርቶታል። ዳግመኛም ሊቁ ቅዱስ ያሬድ፡- "ሳይተክሏትና ውሃ ሳያጠጧት የለመለመች የአሮን በትር በቤተ መቅደስ ነበረች። ለካህናት ዝግጁ ያደረጋት ነበረች። አንቺም በቅድስናና በንጽሕና ጸንተሽ እንደ እርሷ በቤተ መቅደስ ኖርሽ። ከቤተ መቅደስም በክብር በታላቅ ደስታ ወጣሽ። በእውነት የሕይወት ፍሬ የኾነ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከአንቺ ተገኘ። ቅድስት ሆይ! ከመልአኩ እንደተረዳሽው ከወንድ ያለመገናኘት ልጅን አገኘሽ። መልአኩ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ያድርብሻል፤ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል ብሎ ነግሮሽ ነበርና" በማለት አማናዊቷ የአሮን በትር እርሷ መኾኗን አስተምሯል /ቁ.፲፩/። ሰው ኾኖ ካዳነን ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

- ፱. ምልዕተ ክብር ሆይ! ከቅዱሳን ኹሉ ይልቅ ትለምኚልን ዘንድ ላንቺ ይጋባል። ከሊቃነ ጳጳሳት አንቺ ትበልጫለሽ። ከመምህራን፣ ከሐዋርያት፣ ከ፵ አርድእትም አንቺ ትበልጫለሽ። ከሱራፌልና ከኪሩቤል ይልቅ የሚበልጥ የመወደድ የመፈራት ግርማ አለሽ። ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው፡- "ኦ ሙኃዘ ፍስሐ! ፈድፋደ ብኪ ግርማ ራዕይ ዘየዐቢ እም ኪሩቤል እለ ብዙኃት አዕይንቲሆሙ ወሱራፌል ፯ ክነፊሆሙ - የደስታ (የጌታ) መገኛ የምትኾኚ እምቤታችን ሆይ! ዐይናቸው ብዙ ከሚኾን ከኪሩቤል፣ ክንፋቸው ስድስት ከሚኾን ከሱራፌል ይልቅ በምእመናን ዘንድ የመወደድ፣ በአጋንንት በአይሁድ በመናፍቃን ዘንድ የመፈራት፣ በሥላሴ ዘንድም የባለሟልነት መልክ አለሽ" ይላል /ቁ.፳፪/። በእውነት የባሕርያችን መመኪያ አንቺ ነሽ። ለሰውነታችን ሕይወትን የምታማልጅን አንቺ ነሽ። አንድነቱን ሦስተነቱን በማመን አጽንቶ ሥጋዌውን በማመን ያፀናን ዘንድ፣ "ጸጋሰ ሥርየተ ኃጢአት

ይእቲ" እንዲል በቸርነቱ ብዛት ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ አማልጁን። ኃጢአታችንን ከሚያስተሠርይልን ልጅሽ ጽንዕት በድንግልና እመቤታችን ጸጋውን ክብሩን እንዳይነሣን ለምኚልን።

ልመናዋ ክብሯ የልጅዋም ቸርነት ከኹላቸን ጋራ ለዘላለም ጸንቶ ይኑር አሜን።

- ††† *ተፈጸመ* †††